እንኳን ደና መጡ

PDF Compressor Free Version

ማንበብ ለህይወት @worldbook0

pdf መፅሐፍትን በቀላሉ የሚያገኙበት የቴሌግራም ቻናል

እንዲሁም ምርጥ ምርጥ ትረካዎችን ያገኛሉ

ይቀላቀሉን ቤተሰብ እንሁን የሚፈልጉትን መፅሐፍ በቀላሉ ያግኙ



ሐሸማል

PDF Compressor Free Version

ማንበብ ለህይወት



ማንበብ ለህይወት ብላቹ ሰርች ብታደርጉ pdf መፅሀፍ በነፃ ታገኛላችሁ

ከ ማዕበል ፈጠነ

PDF Compressor Free Version

ሐሽማል

ከማዕበል ፈጠነ

PDF Compressor Free Version

ይህ መጽሐፍ ጥበባዊ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የሰረቀም፣ያሰረቀም ተከታትሰዉ እንጦርጦስ ይወርዳ

ማዕበል ፈጠነ ፳፻፲፩ ዓ.ም

1ኛ ዕትም ሐምሌ 2011

2ኛ ዕትም ሀዳር 2012

3ኛ ዕትም ካቲት 2012

4ኛ ዕትም ሰኔ 2012

5ኛ ዕትም ነሐሴ 2012

ፕልስቱ

በሌሊት ትገይስ መንፈስየ

ነቢከ እግዚኦ አምላኪየ።

አከፋፋይ፡ ዘውዱ ቤተ መጻሕፍት

0911587537/ 09 20 64 12 01

2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

PDF Compressor Free Version

መግለጫ

እንደማይቆጠሩት የሰማይ ከዋክብት የማይሰፈር ጥበብ በአባቶቻችን የልብ ግድግዳ ተሰቅሏል። ከትውልዱ ርቃ የተሰቀለውን ጥበብ ቁመተ ጀርጋዳው የማዕበል ፈጠነ መጽሐፍ በቅኔ ክንዱ ታቅፎ አወረደልን። ንግሥት ሳባ ሰሎሞንን የፈተነችበት የጥበብ እንቆቅልሽ ይህ ይመስለኛል፤ ከዚህ በኋላ ጠቢቡ ሰሎሞን ዝናዋን ሰምቶ ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ እንጂ ኢትዮጵያ ወደ እርሱ አትሄድም፤ ከሰሎሞን የሚበልጠው ይህ ነውና!ይህ መጽሐፍ በዘመናዊ ትምህርት ብቻ ተሳፍሮ ከኢትዮጵያ ፍልስፍና የወጣውን ትውልድ ወደ ኢትዮጵያዊ እሳቤ የሚመልስ ባለክንፍ መርከብ ነው። ከተዋነይ የሕይወት መንገድ መቀላቀል ለሚሹ የሕይወት መንገደኞች የተዘረጋ የጥበብ ድልድይ እነሆ!!

ሊቀ ሊቃውንት ስምዐ ኮነ መልአክ

PDF Compressor Free Version

መግቢያ

አምናና ታች አምና ለዐሥሩ ጣቶቼ ሥራ አልነበራቸውም። ሰኔና ጣቶቼ ሥራ ፍለጋ ደጋ ስወጣ፣ ቆላ ስወርድ ከዓመታት በፊት ነበልባል የሚባል የቅኔ ዘራፊ

"በቅኔያችን ጥበብ በያዝነው ሆሣዕና፣

እንነጠቃለን በግዙፍ ደመና"

ከሚለው ቅኔ "ጥበብ ተቀብራለች" ብሎ የነገረኝ ትዝ አለኝ። ቅኔዉን ከልጅነቱ ጀምሮ እኔም አውቀዋለሁ። የሊቁ ክፍለ-ዮሐንስ መወድስ ነው። ሊቁ ክፍለ-ዮሐንስ በዘመኑ ባንዲት ዕለት፣ በተመሳሳይ ሰዓት በጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴና በሸዋ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቅኔ-ማኅሌት ሲያገለግል ይውል ነበር። በዚህ ጊዜ የሸዋ ሊቃውንት ሊቁ ክፍለ-ዮሐንስ ከእነሱ ጋር በመንፈሳዊ አገልግሎት እንደ ዋለ በኩራት ሲናገሩ የጎንደር ሊቃውንት ደግሞ በጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴ እንደ ልማዱ አዳሩ ልብሱን ለብሶ ቅኔውን ሲገጪው መዋሉን ይናገራሉ። ባለ ቅኔዉ በተመሳሳይ ሰዓት ጎንደርና ደብረ ብርሃን ሥላሴ በመንፈሳዊ አገልግሎት ስለማሳለፉ ሲጠየቅ፡-

"ንሕነሂ በማብረ ቅኔ ዘበሆሣዕና፣

PDF Compressor Free Version

አምአደ ገፋዒ ወተገፍዒ ንትመሰጥ በደመና" ሲል በመወድሱ መሰሰ። ቅኔው ከላይ ከላይ ሲተረጎም፤

‹‹ብቅኔያችን ጥበብ በያዝነው ሞግዕና፤

እንነጠቃለን በግዙፍ ደመና" እንደ ማለት ነው። ነበልባል እንደ ነገረኝ በዚህ ቅኔ ውስጥ ጥበብ ተጥበራለች"

ነበልባል ሌላም ተመሳሳይ ታሪክ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር።

"ከኢትዮጵያውያን ጠቢባን ሌላው ደግሞ ተዋነይ ይባል ነበር። ጠቢቡ ተዋነይ ከጎጃም ቅኔ ተቀኝቶ በተመሳሳይ ሰዓት ጎንደር ይደግም እንደ ነበር ዜና-ጥበቡ ይጠቁማል። ይህንን የኢትዮጵያ ዕውቀ ድንቅ ጥበብ የቅኔ ሊቃውንት በኩራት ይናገሩታል።

ባላገሮችም

‹‹ተዋነይ በጣና

ይመስላል ደመና" ሲሉ ተዋነይ በደመና መጋለቡን ይተርኻሉ" ብሎኛል-ነበልባል።

ነበልባል የነገረኝን ምሥጢር ለዐሥሩ ጣቶቼ ነገርኋቸው። ሥራ እንደ ፈጠርሁላቸው ቆጠሩት። ከዘመናት በፊት የነበረውን ሀገራዊ ፍልስፍና እየተሻመ መክተብ ጀመሩ። ባለ ቅኔው ክፍለ ዮሐንስ መጣ። ተዋነይ ተገለጠ። ሌሎችም ሊቃውንት በየተራ መጡ። አሥሩ ጣቶቼ በቅኔው ውስጥ የተቀበረውን ምሥጢር ሀገርኛ ብዕር፣ ጨብጠው መክተብ

PDF Compressor Free Version

ሲጀምሩ ጠቢቡ ሑሬ ኩራዝ ለኮሱ። ወዲያው ግን ነፋስ በቤቱ ቀዳዳ
ገብቶ አጠፋባቸው። ሊቅ ዐፅቁ ሐሸማል የሚባል በጨለማ ውስጥ ቀደ
ብርሃን የሚፈነጥቅ መጽሐፍ ይዘው ብቅ አሱ። ሐሸማል ድቅድቁን
ጨለማ ገፈፈው። ዐሥሩ ጣቶቹ ሲስተቡ አኔን እንቅልፍ ጣለኝ። ስነቃ
ጠቢቡ ሑሬ ተሰውረዋል። ሊቅ ዐፅቁም ሐሸማልን ይዘው ከቤት
ወጥተዋል። ዐሥሩ ጣቶቼ አንድ መጽሐፍ ጽፈዉ ስለ ስሙ
ሊጨቃጨቁ ደረስሁ። ስሙን ሐሸማል በሉት አልኋቸው። ሐሸማል
ብለው ጠሩት። እነሆ ሐሸማል ሆነ!!

ማዕበል ፈጠነ

PDF Compressor Free Version

ከዘመናት በፊት ውቢቱ ኢትዮጵያ በሊቃውንት ተጥለቀለቀች። ታላቋ ከተማ ጎንደርም በሊቃውንት ቅኔ ክብሯ ተወሳ። የሊቃውንቱ እግር ወደዚያው ፈጠነ። ሰማዕቱ ኖላዊ በጎንደር ከተማ ለማስተማር ደፋ ቀናማለት በዛባቸው። እግረ መንገዳቸውንም ከጎንደር ምሥጢራዊት ውኃ እየቀዱ ወደ ፊት ትልቅ ሰው ሆኖ ሀገር ይጠቅማል፣ ወገን ይረዳል ላሉት ያድሉ ያዙ። ምሥጢሩ ከእሳቸው አልፎ ከባዕድ ጀሮ እንዳይደርስ እየተጠነቀቁ ሲያድሉ ዓመታት አለፉ። ቀስ በቀስ የጎንደር ልዕልና በጠቢባን ልሳን ተወራ። ክብሯ የጸሐፍት ድርሳናትን አጨናነቀ። ምሥጢራዊው ሊቅ ኖላዊም እንደ ቅድመ አያቶቻቸው እንደ-ክፍለ ዮሐንስ በደመና እየተንቀሳቀሱ ጭምር ስለጎንደር ልዕልና፣ ስለ ኢትዮጵያ ረቂቅ ፍልስፍና ባራቱ ማዕዘን ላሉ ሀገርኛ ሊቃውንት ሹክ አሉ። ጭምጭምታው ከምዕራባውያን ብልጥ ጆሮ ደረሰ። ምዕራባውያን ቁስ መስለው መስቀል ጨብጠው ኢትዮጵያን ከመውረር በማይተናነስ መልኩ ሰፈሩባት። በተካላተፈ ቋንቋቸው፣ በአዳዲ ምላሳቸው የውሸት ስብከት መስበክ ጀመሩ። ዳር ዳሩን እየሰበኩ መኻል ጎንደር ሲደርሱ የጎንደር ሊቃውንት 'የቀበሮ ባሕታዊ ከበግ መኻል ይሰግዳል' ሲሉ ዘበቱባቸው። ተልእኳቸው እንደ ከሸፈ ሲረዱ የስብከታቸውን መርሕ አስተካከሉ። በተለይ ጀርመን ከኢትዮጵያ የግእዝ ሊቃውንትን አጥብቃ እንደ ምትፈልግ ለንጉሡ አስረዱ። ንጉሠ-ነገሥቱ ባራቱ ማዕዘን ያሉ ሊቃውንት እንዲጠሩ አዋጅ ነገሩ። የደከመ በምርኩዝ፣ የታመመ በደጋፊ

PDF Compressor Free Version

እየታገዘ በሳምንት ቤተ-መንግሥቱ ቅኔ ቤት ሆነ። ከጎንደርም ሊ
ኖላዊን ጨምሮ ዐራት ሊቃውንት ተጠርተው ነበር። ሦስቱ ወደ ጎንደ
ሲመለሱ ንጉሡ ታዋቂውን ሊቅ ኖላዊን ወደ ጀርመን ልከው ጀርመን
በግእዝ እንዲያበለጽጉ አዘዙ። ተልእኮው እውን ሆነ። ሊቁ ጀርመ
ሲገቡ ጀርመናውያን አደባባይ ወጥተው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላ
እያውለበለቡ ተቀበሏቸው። የሊቁ ፎቶ-ግራፍ በጀርመን ከተሞ
ከዚያም ከዚያም ተሰቀለ። ቡታንጣለለው የጀርመን ቤተ-መንግሥ
የእራት ግብዣ ላይ ተገኝተው መወድስ-ቅኔ አሰሙ።

ሊቁ ከሳምንት በኋላ ግእዝ ቋንቋ በማስተማር ተጠመዱ። የጀርመ
ምሁራን ከጥቂቱ የሐበሻ ሊቅ እግር ሥር ተኮለኮሉ። ሐበሻን እን
ጥቁር ውሻ የሚቆጥሩ ነጮች ለዓላማቸው ሲሉ ቍንጽል ቀበሮ መሰሉ
ሊቁም ቀያይ ቀበሮዎችን ግእዝ ቋንቋ ማስቆጠር ጀመሩ። ቀያ
ቀበሮዎች ግን ከግእዙ ትምህርት ይልቅ ስለ ኢትዮጵያ የጥንት ጥበ
ሲጠይቁ ሀገራዊ ምሥጢር ላለመግለፅ ሊቁ ሲሸሹ ኖሩ።

ከዓመታት በኋላ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ሲዘጋጁ በድንገ
ሕይወታቸው አለፈ። ሕልፈተ-ሕይወታቸው እንደተሰማ እኔ አባ ደመ
ጎንደርን እየዞሩ ለፈፉ። አስከሬናቸው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ለብሶ
ጎንደር ሲገባ ጠቢባን በተለያየ የሥራ ዘርፍ ተጠመዱ። ቀብራቸው
አጨቃጫቂ ሆነ። መላ ጎንደር ተሰበሰበ። የጀግኖች ማኅበር በጀግኖ
ወግ እንዲቀበሩ ወሰነ። ሊቃውንቱ በሊቃውንት ወግ መሆን አለበት ሲለ
ውሳኔውን ሻሩ። ጠቢባኑ በጠቢባን ወግ እንዲሆን ዲኑ ታጥቀው
ተከራከሩ። ይህንን ተከትሎ በጎንደር ከተማ ጭቅጭቅ ተፈጠረ። ነገሩን

PDF Compressor Free Version

የማፊቱ አንገሬ ሲቃውንት ተመረጡ። ከሲቃውንት ክፍል ሊቅ ዕዕቁ ተወክሱ። ከጀግኖች ማኅበር በኩል ደግሞ ዐራትጀግኖች ተመረጡ። ከጠቢባኑ ድንቁ ዘጎንጅ ተገኙ። ጉባኤው በገነት ተራራ እንዲሆን ወሰኑ። በገነት ተራራ ላይ ተደረገ።

ጠቢባኑ ወደ ገነት ተራራ ሲያመሩ ብልኮ ሰፈር ሲደርሱ ሁሉም ነገር በዝምታ ተሸብቧል። የብልኮ ባሕላዊ ቤቶች በዝምታ ተለጉመዋል። የብልኮ አታሞ ወዲያ ተከላትማ ወድቃለች። የምሽት ቤቶችን በመሰንቆ የሚያጠምቁ አዝማሪዎች ብልኮን እስከ ወዲያኛው የረሷት ይመስላሉ። ብልኮ እንደ ጣና ገዳማት በጸጥታ ተውጣለች። የመሰንቆም ሆነ የአታሞ ድምፅ አይሰማባትም። ባሕላዊ ቤቶች የባሕሉን እያደረሱ አይደለም። በባሕል ምሽት አንድ ብርሌ ጠጅ በስሙኒ እንዳልሸጡ ከንግድ ዓለም መንነዋል። ፀሐይ ወደ መስኮቷ ስታቁለቀቁል ጠቢባኑ በአንድ አሮጌ ጋሪ ታዝለው ከዐጤ ቴምድሮስ አደባባይ ወደ ገነት ተራራ አዘገሙ። ባለጋሪው የሲቃውንቱን ሻሽ ሲመለከት ሙዚቃውን ዘግቶ መዝሙር ከፈተ። ጠቢባኑ ግን ለመዝሙሩም ሆነ ለሙዚቃው ጆሮ የሰጡት አይመስሉም። በዚያውም ላይ የጋሪው ጎማዎች በጠጠሮች መንፈራገጥ ሲጀምሩ የመዝሙሩ ለዛ ጠፋ። ዘማሪው ጥሩ ድምፃዊ ቢሆንም የዜማው ጣዕም ከጋሪ ካኻታ ጋር ሲደመር ቃናው ከሰመ። ባለጋሪው ለሙዚቃውም ሆነ ለመዝሙሩ ትኩረት እንዳልሰጡት ሲመለከት ድምፁን አጥፍቶ እየተጠማዘዘ ቀጥታ ወደ ገነት ተራራ አመራ። ጋሪው በሲቃ ገነት ተራራን አቋርጦ ወደ ቁንጮው ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው እንዲያቆም ምልክት ሰጡት።

PDF Compressor Free Version

ባለጋሪው ዳገቱን ሳይፈጽም እንደ ምንም ብሎ ፈረሱን አስከ ጋሪው ገታ። አሣውንቶች ቀስ ብለው ከወረዱ በኋላ ሰባስ ጋሪው ከከሳቸው እየመገሥለጡ ስሙኒ ስሙኒ ሳንቲም ሽጎጡለት። ባለጋሪው አሮጌ ፈረሱን ወደ ኋላ መልሶ ሲፈተለክ ታሪክ ነጋሪዎቹ ገነት ተራራ ላይ ወጥተው ጉብ አሉ። ሰዓቱ ተጓድቶ ምድር መሽቶ ነበር።

ጉባኤው እንደተጀመረ ከጅግኖች ማኅበር ወገን በቀብራቸው ቀን ትልቁ ሰውሲቅ ዐፅቁ መድኅ፡ መተኮስ እንዳለባቸውና ቀብሩም በጅግኖች ማኅበር ወግ እንዲሆን የጀግኖች ማኅበር ሲወስን ሲቅ ዐፅቁ ሐሳቡን በሐሳብ ለመሻር መቋሚያቸውን ተደግፈው ተነሡ። ሲነሡ ወገባቸው ቀ...ሽ...ቀ...ሽ ሲል ተሰማ። በኖሬ የደቀቀ የካህን ወገብ ይህንን መሰል ድምፅ ማሰማቱ የተለመደ ስለሆነ ብዙ አትኩሮት የሰጠው አልነበረም። መምሬ ገጸቸውን በመስቀል አማትብው፣ዐራቱን ማዕዘን ባርከው፣ በሰባቱ ሰማያት አምላል የተፈጠሩ ሰባቱን የጎንደር ተራሮች ቃኝተው መናገር ጀመሩ።

"በቅድሚያ ሰማዕቱ ናሳዊን አስመልክቶ ስለተናገራችሁት ጠቃሚ ሐሳብ ክልብ ክልብ አመሰግናለሁ። የተናገራችሁትን ሁሉ ገቢራዊ ለማድረግ ግን የሃይማኖቱ ሥርዐት አይፈቅድም። በፈቅድልኝ ኑሮ መድፉን መተኮስ ቀላል ነበር። ግን እንኳን መተኮስ ባርኮ መስጠት ክልክል ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን የድሮ ፋሽስት ጳጳሳት አይደለንም። ቀኖናችንም አይፈቅድልንም...::" ብለው ትንሽ ስለ ክብረ ክህነት ተናገሩ።

የክብረ ክህነቱን ምሥጢር ዘርዝረው አስረድተው እንዳበቁ፤

PDF Compressor Free Version

"ቀኖናው በሚፈቅደው መሠረት እንጂ በዘፈቀደ ደግሞ የሚሆን ነገር የለም። ሲቱ ኖላዊ አርበኛ መሆናቸውን ወዳጃቸው ቀርቶ ጠላታቸው ይመሰክራል። በጠላት ወረራ ጊዜ ከታቦቱ ጎን ሆነው፣
ኢሳቱ የሀገሬ ጀግና፣
እየፎከረ ይገላል ገና እያሉ አጽንዖት ሲሰጡ አርፍደው ወደ መጨረሻ አካባቢ ከአባት አርበኖች እኩል ተሰልፈው ተዋግተዋል። ድል መተዋል። ያን ጊዜ እኔም እንደ ዐቅሜ በዲቁና እያገለገልሁ ቃጭል እያቃጨልሁ አብሬ ነበርሁ። ተዋግተዋል። ማርከዋል። በከባዱ ቆስለዋል። እግራቸው ግድም እንደተመቱ ትዝ ይለኛል። ተመተው ግን አላፈገፈጉም። ከጠላት ለተወረወረ አጸፋ መልሰው ያንን የመታቸውን ወታደር እስከ መሣሪያው ማርከው በምሕረት እንዳለፉት ትዝ ይለኛል። እንደ ጌታችን ማርኮ መማር ያስተማሩ መምር እየተባሉ ሲመሰገኑ ሰምቻለሁ። ይህን አውቃለሁ። ቁስላቸውን በዐይኔ በብረቱ ተመልክቻለሁ።" ብለው እንባ ቀድማቸው። በመሐረባቸው ጫፍ ዐይናቸውን ጠርገው ተረጋግተው እንደ ገና መናገር ጀመሩ።
"እኔን ያሳሰበኝ የመድፉ ሳይሆን የጸሎቱ ጉዳይ ነው። ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ጀምሮ የሚጸለይ መጽሐፍ አለ። መዋቲው ከሞተበት ቅጽበት ጀምሮ የሚጸለይ መጽሐፈ-ሙታን ነው። መጽሐፉ ኩበሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተውጣጣ ሲሆን ለሙታን ብቻ የሚጸለይ የተለመደው ነው። ጸሎቱ ለሙታን የሚጸለይ ሲሆን፣ የተለያዩ የማዕረግ ክፍሎች አሉት። የምሁርና የመነኩሴ፣ የሴትና የወንድ በሚል አንቀጽ ተከፋፍሏል። ይህ የወረቱ መጽሐፍ የሚያዝዘው ክፍል ሲሆን

PDF Compressor Free Version

የብራናው ግን የሊቃውንት፣ የፈላስፎችና የጠቢባን ክፍሎችን ይጨምራል። በእውነት ሊቱ በአርበኞች ወግ ይቀበሩ ቢባል ይህ ሁሉ ቀኖና ይፋለሳል። መቼም 'ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ' እንደሚባለው ሁሉ ለስማዕቱ ያልሆነ ብራና ባዶ ቁርበት እንጂ በምሥጢራዊ ቀለም የታጨቀ ምሥጢራዊ ብራና ሊሆን አይችልም። ስለዚህ በቀብሩ ጊዜ ለንባብ የሚቀርበው የብራናው መጽሐፍ ነው። መቼም ሰሊቁና ለስማዕቱ ክብር እንኪን በብራና ሌጦ፣ በድንጋይ ሰሌዳ፣ የተጻፈ ቀለም እንደማይነልጣቸው እመን ነው። መጻሕፍት ሁሉ ተሰብስበው ቢነበቡ ያንሱባቸዋል እንጂ አይበዙባቸውም። የሊቁንና የሰማዕቱን ክብር በትክክል ይገልጣሉ ብዬ አፈን ሞልቼም አልናገርም። ተነብበው ቀርቶ አፍ አውጥተው ቢመሰክሩ እንኳን ክብራቸውን አይገልጡም። የሆነው ሆኖ በአባታቸው በዐጤ ፋሲል ዘመን ተጽፎ፣ በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት የተተረጎመው የማእዙ ብራና መቅረቡ አይቀርም። ያንን ብራና እንዲያመጣ የመጻሕፍት ክፍል ኀላፊዉን አዝዠዋለሁ። ብራናው ሲወጣ ከብዙ ሞጭላፊዎች ዐይን ውስጥ እንደሚገባ አላጣሁትም። ቢሆንም 'ሕልም ተፈርቶ' እንደሚባለው ሌባ ተፈርቶ ሊቀ-ሊቃውንቱን በወረቀት በተጻፈ መጽሐፍ ጻልየን አንሸኛቸውም። ጥቅልሉ ብራና መቅረብ አለበት።" አሉ።

"ይህ መጽሐፍ ከሌሎች መጻሕፍት በምን ይለያል?" አለ አንድ ሰው ከመኻል ጣልቃ ገብቶ።

"መጽሐፉ ሐሽማል ይባላል። ትርጉሙን እንዳትጠይቁኝ። ይህ መጽሐፍ ከተለመደው ላይ ሁለት ነገር ይጨምራል።" ይህ መጽሐፍ

PDF Compressor Free Version

"ምን ምን?" አለ ጠያቂው ሰውዬ።

"ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በወረቀት የታተመው መጽሐፍ የጠቢባኑንና የሊቃውንቱን ክፍል አያካትትም። በሀገራችን ሊቃውንት በምሥጢራዊ ቀለም የተጻፈው የኖንቱ ብራናው መጽሐፍ ግን የጠቢባኑንና የሊቃውንቱን ክፍል ይጨምራል።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ሲመልሱ።

"ታሉስ ይሰውጣል? ወይስ በወረቀትና በብራና ላይ መጣፉ ነው ልዩነቱ?" አሉ ያው ቄስ ቀመስ አረጋዊ ማብራሪያው በደንብ ስላልተረዳቸው።

"ቀለሙም ልዩ ነው።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ።

"ቀለሙም ልዩ ነው። ልዩ ነው ማለቴም የጎበረ ቀለማቱን ዝርዝር ቀይ ጥቁር ነጭና ቢጫ መልክ ይገልጣል ለማለት አይደለም። አባቶቻችን ለመጻሐፉ የተጠቀሙት ጎበረ-ቀለም ውስጠ ወይራ ነው ማለቱ ነው።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ኮስተር ብለው።

"...ለምሳሌ ጠቢባን ሲያርፉ 'ልብየ ርእየት ብዙን ጥበበ' የሚለው ክፍል ይነበባል። ትርጉሙም 'ልቤ ብዙ ጥበብ ናፈቀች' ማለት ነው። ሊቃውንት ሲሞቱ ደግሞ 'ተጎጥኦ ሊቅስ እኩይ ውእቱ' የሚለው ሸካራው ክፍል ጎላ ባለ ድምፅ በጥሩ አንባቢ ይነበባል። ትርጉሙና ንባቡ ፈታኝ ነው። ውሽክሽክ ቄስ ሊያነበው አይችልም። ከታወቁ ሊቃውንት በቀር ውሽክሽክ ቄስ ሲይዘው መጽሐፉም ዝም ቄሱም ዝም ናቸው። አይጣጣሙም። መጽሐፉ በእውቀት የበሰለ ብራና ላይ የሰፈሩ ቀለማትን በወረቀት ከሠፈሩ ቀለማት ለይቶ የሚያነብ የንስር ዐይን ያለው ሊቅ ይጠይቃል። ዛሬ ዛሬ ብራናውን መጽሐፍ ቀርቶ ወረቀቱን አቃንቶ

PDF Compressor Free Version

የሚባነብ አንደበተ-ርቱዕ ሊቅ ማግኘት ዘበት ሆኗል አንደበተ-ርቱዕ ሰባኪ እንጂ:: አዎ! ሰባኬዎች እንደ አሸን ፈልተዋል:: መቅረዞች ግን ተሰብረዋል:: የአብነት ትምህርት እየላላ፣ ለውሽክሽኩ ትውልድ ሲባል ፈታኝ ፈታኝ መጻሕፍት ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተርጉመው አልቀው ቁሱን ሁላ ውትልፍ ቢጤ አድርገውታል:: የድሮ መምህራን ጠጅ በጉሮሯቸው እየተንቈረቈረ እንኳን አእምሯቸው ጠጣር ነበር:: የዛሬው ትውልድ ግን አእምሮው ቀርቶ ምላሱ ላልቷል:: በከፊልም ቢሆን አእምሮው ላልቶ፣ ምላሱ ስልቶ፣ ቀለም አይቆነጥጥም:: በዚያም ላይ ሐሽማል በቃሁ፣ ነቃሁ፣ የሚል ቀለም ሳይገድፍ የሚያነብ ሊቅ ይፈልጋል::" ዐፅቁ ማዶ ማዶውን አማተሩ::

ጠቢባኑ በውስጣቸው ፈገግ አሉ::

የጀግኖች ማኅበር ተወካዮች ግን በደንብ ስላልገባቸው ፊታቸው ጨፍግጓል::

"መጽሐፉስ ይምጣ! ታዲያ አንባቢው ማን ነው?" አሉ እንደ ቄስ የጠመጠሙት አዛውንት ድንቁንና ሊቅ ዐፅቁን እየተመለከቱ::

"ታሪኩ የሚባል ወጣት ሊቅ መርጫለሁ::" አሉ ሊቅ ዐፅቁ::

"ታሪኩ? ታሪኩ? ማን ነው እሱ ታሪኩ?::" አሉ ሰውየው::

"የእኛው ልጅ ነው:: የኢትዮጵያን ታሪክ እያጠና ሲጽፍ የሚውል በእድሜ ለጋ፣ በእውቀት ትልቅ ልጅ ነው:: መቼም ፍጻሜውን አንድዬ ያብጅለት እንጂ አያያዙ የወግ አይደለም:: ታሪክ ተናጋሪነቱን ተረድቼ ስሙንም ታሪኩ ብየዋለሁ:: ተንጠባጥበው ጥንት ሳይጻፉ የቀሩ

PDF Compressor Free Version

የኢትዮጵያን ታሪክ ... የሚጽፍ ሊቅ ልጅ ነው፡፡" አሉ ሊቅ ዐፅቁ፡፡

"የኢትዮጵያ ታሪክ ተጽፎ ያልቅ ብሎ ነው?" አሉ ድንቁ እያደነቁ፡፡

"ባያልቅም የድርሻውን እየሠራ ነው፡፡ የጎንደርንም ታሪክ ከልሙጥ ድንጋይና ከብራና መጻሐፍት እያሠሠ፣ እየበረበረ፣ እውነቱን እያመሳከረ ሲጦምር ሳየው ደስ ይለኛል፡፡ "ስም ይመርሖ ኀበ ግብሩ" እንዲሉ አበው ስምና ሥራ በእሱ ላይ ተስማምተዋል፡፡ ደምቀዋል፡፡ በእርግጥ ብዙኃኑ የሚያውቁት "ኩለሄ" በሚባል ስሙ ነው፡፡ ከዚሁ ጎንደር ውስጥ ቅኔ በመማር ላይ የሚገኝ ሲሆን እስካሁን መላ-ጎንደር አያውቀውም፡፡ ልጁ ግን ከሊቁ ጋርም ትንሽ የሥጋ ዝምድናም አለው፡፡ የአባቴን አብነት መጨበጥ አለብኝ ብሎ አንገቱን ደፍቶ ሲማር ይኖራል፡፡ ወደ ፊት ዐራት ዐይና ሊቅ ሆኖ ለሀገር ይጠቅማል ብዬ አስባለሁ፡፡ ከዛሬው ቅኔውን ሲሰልቀው፣ ትርጓሜውን ሲየደቀው፣ እንባ ያስመጣል፡፡ ሊቅ የሚለው ቋንቋ አይገልጠውም፡፡ ልበ-ብርሃን ነው፡፡ መፍቀሬ-ታሪክነቱን ዐይቼ ስሙን ታሪኩ አልሁት፡፡ ብርሃን ልለው አስቤ ነበር፡፡ ብርሃን የተለመደና ቀላል ስም ስለ መሰለኝ ታሪኩ ብየዋለሁ፡፡" አሉ ሊቅ ዐፅቁ፡፡

ሁለተኛው ተናገሪ በእንግድነት የተገኙት ድንቁ ዘጎንጅ ደብረ-ጥበብ ነበሩ፡፡ በዚች ቀን አነጋጋሪዉ ሊቅ ድንቁ እንደ ተዋነይ በደመና ተጭነው፣ ለልቅሶ ወደ ጎንደር በነፋስ ፍጥነት እንደሄዱ ተወርቶባቸው በጥብቅ ሲያስተባብሉ ሰንብተዋል፡፡ ከጉባኤውም ሆነ ከቀብሩ ግን ተገኝተዋል፡፡

በመጨረሻ ለመናገር እጃቸውን ሲያወጡ ተፈቀደላቸው፡፡

PDF Compressor Free Version

የተዋነይ የቀለም ልጅ ድንቁ ቀጠሉ።

"የተነሣው ሐሳብ ሸጋ ነው። ሸጋ ሐሳብ ሲነሣ ጊዜ ደስ ብሎኝ በተመሥጦ አዳምጥ ነበር። እናም ሊቅ ዐፅቁ እንዳሉት ጸሎቱ በሐሸሻል መጽሐፍ ይነሄዳል። በዚህ እስማማለሁ።

"የእኔ ሐሳብ በነፍስ ዓለም ጀግናና ሊቅ ያው አንድ ናቸው የሚል ነው። ሲቁም ሆነ ጀግናው በጌታችን ፊት ቆመው መለኮታዊ ፍርድ ይቀበላሉ። ክፍተት የሚፈጥረው የፍትሐቱ ጉዳይ ነበር። ይኸውና ሊቅ ዐፅቁ በሚገባ ተነተኑት። በሊቅ ማዕረግም ሆነ በጠቢባን ማኅበር ወግ ቢቀበሩ አንድ ነው። ግድ የለም። መናገር የምፈልገው መጽሐፋቸውን አብራችሁ አንዳትቀብሩ ነው።" ብለው ዐይኖቻቸውን ወደሊቅ ዐፅቁ አነጣጠሩ።

ሊቅ ዐፅቁ ረስተውት የነበረው የመጽሐፋቸው ጉዳይ ሲነሣ አንድ ነገር አብሮ ትዝ አላቸው። ከመጽሐፋቸው አንዱ የሕይወት ውኃ ረቂቅ እንደ ሆነ ፈኖኖ ሲመጣላቸው አንነታቸውን አወሣወሡ። በግእዝ ቋንቋ ማየ ሕይወት ይባላል።

ድንቁ ወልደ-ተዋነይ ግን ድንት ንግግራቸውን ቀጠሉ።

"ቀደምት አባቶቻችን ምእመናን ሲያርፉ አጃቸውን ከሐፍረተ-ሥጋቸው ላይ ጥሰው ይሸፍኗቸዋል። በአንድ ሴት ጸንተው መኖራቸውን ሰመግለጥ ነው። ደናግል መነኰሳት ሲያርፉ ደግሞ እጀታቸው ከዐይኖቻቸው ላይ ያርፋሉ። ይህንን ዓለም ዐላዩበትም ስማሉት ነው። አስኬማቸው ከራሳቸው አይወልቅም። ሲታውኑት ሲያርፉ ደግሞ እጃቸው በትእምርተ-መስቀል ሆኖ ግንባራቸው ላይ ይዘረጋል።

PDF Compressor Free Version

ከዚያም ግንባራቸው ላይ መጻሕፍት ተነባብረው ይደረደራሉ። አብረው ይከራናሉ። አብረው ይቀበራሉ። ብዙ የሀገራችን ሊቃውንት ሲሞቱ ግዙፍ ግዙፍ የሆኑ መጻሕፍተ-ጥበብ ድራሻቸው የጠፋው አብረው ግብአተ-መሬት ስለሚፈጸምባቸው ነው።

"ለነገሩ...?" አሉ ድንቁ ሰባቱን የጎንደር ተራሮች በአንክሮ እየተመለከቱ። "...ለነገሩ መጻሕፍትን ጠባያቸውንና ግብራቸውን ከማያውቅ ሕያው ሰው እጅ ላይ ከመጣል ከሊቃውንቱ ጋር አብሮ መቅበር ሳይሻል አይቀርም። የእነ-ተዋነይ በደመና የመጫን ጥበብ፣ የነ-ሊቅ አፅቁ ቀዳማዊዉን ከበጋ ሰማይ ላይ ዝናም የማውረድ ጥበብ፣ የነደብተራ አውግቸውን በጨለማ ውስጥ ያለመብራት የሚነበብ መጽሐፍ ለመጻፍ የሚያስችል ቀለም፣ ለመሥራት የሚያስችል ጥበብ የተሸከመ መጽሐፍ አብሮ እንዳይቀበር ብለን አስቀርተን ዛሬ የት እንደደረሰ እንኳን አይታወቅም። ሀገራችን ታድግበታለች ብለን አስቀርተን ምሥጢሩን ከማያውቁ ሰዎች እጅ ሲገባ ውፍድፋዱን አጠፉት። በክርክር ፊት የተገኘ የማሸለ ማሳና ባልተማሩ ሰዎች እጅ የሚገቡ መጻሕፍት አንድ ናቸው። ምንም ሳይጠቅሙ ድራሻቸው ይጠፋል። ዛሬ እንደምታዩት በመጻሕፍቱ ተመራምረን ከምናገኘው ሀብት ይልቅ መጻሕፍቱን ሸጠው፣ የሚያገኙት ሀብት እየማረካቸው ሰነፍ-ልብ ያላቸው ሰዎች መጻሕፍቱን ሸጠው ጨረሱብን። ሀገር በጥበብ እንጂ በገንዘብ የምትለማ መስሏቸው የአባቶቻችንን ጥበብ በገንዘብ ለወጡብን። ይሄው በፊረንጅ ሀገር ልሳናቸው ተዘግቶ፣ የተቀመጡ የጥበብ መጻሕፍት ምስክሮች ናቸው። ስንት አያሌ መጻሕፍት በገዘምታ ከሰው ሀገር በስደት ይቅበዘበዛሉ።

PDF Compressor Free Version

ዛሬም ከኢትዮጵያውያን በስተቀር ለማንም ልባቸውን ላይሰጡ ቃል የገቡ ይመስላሉ-መጻሕፍቱ። ፈረንጅ በጠቀምባቸውም እንኳን የላይ የላዩን እንጂ የልባቸውን ጥበብ ከኢትዮጵያውያን በስተቀር ለማንም ላይሰጡ ተማምለዋል። ጥበባቸውን በጉያቸው ደብቀው ይዘዋል። የተጻፉበት ቀለም ንልህ ፊደሱን እንጂ፣ ረቂቅ ምሥጢሩን፣ ለማንም እንዳይሰጣ በጠቢባን የጥበብ ቁልፍ ተክርችሞ ተዘግቷል። ሥራ ላይ ያሉ በህጊ ቤት ያሉ መጻሕፍት ብቻ ናቸው። እናም በህገር ቤት ያሉ መጻሕፍት ክሙታን ሊቃውንት ጋር እንዳይቀበሩ እማጸናለሁ። ይህ ስሕተት እንደሆነ አምናለሁ። አንድ ሊቅ ስንቀብር አንድ መጽሐፍ አብረን እየቀበርን ክሄድን ህገር እንደመቅበር ይቆጠራል። ደግሞ እውነት ነው። ቅድስት ኢትዮጵያን አብሮ መቅበር ነው። አባታችን ናላዊም አያሌ መጻሕፍት ጽፈዋል። ወደ ሠላሳ አምስት ላይደርሱ ይቀራሉ? ደርሰዋል። በሐዲሳቱ ልክ ሆነዋል። ደግሞ መጽሐፎቻቸው የሞላ አይደሉም። በምሥጢር የተሞሉ እንጂ። የቀለም ጓደ ስለነበሩ ይህን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ስለዚህ እኒህ ሁሉ ዐበይት መጻሕፍቶቻቸውን አብራችሁ እንዳትቀብሩ ስል በትሕትና እማጸናችኋለሁ።" ብሎው ጎርደደ ጎርደድ አሉ።

ሊቅ ዐፅቁ በአምንታ ራሳቸውን አወዛወዙ። በአምላለ-ካህን ተንጎራደው ሲመለሱ "ስለመጽሐፎቻቸው ይህንን ያክል ካልሁ ሌላ አንድ ቀላል ነገር ይቀረኛል።"

"እሺ!" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ዜማ ባለው ድምፅ።

"አሥ አቀጥላለሁ።" አሉ ድንቁ።

PDF Compressor Free Version

"በጎንደር አንድ ሊቅ ሲኖር በክብር ነው። ሲያርፍ ደግሞ ሊቁን ብቻ የሚመጥኑ በጎንደር ሊቃውንት አንደበት ብቻ የሚደረሱ ውኃ ያልነካቸው ወረቦች ይፈጠራሉ። ለሊቁ ክፍለ ዮሐንስ የተደረሱ መዋሥዕቶችና ወረቦችን የመሰሉ ዘመን ተሻጋሪ ድርሰቶች ዛሬም መደገም አለባቸው። በቅኔው በክል ግን አዲስ ቅኔ፣ አዲስ መወድስ፣ መፋጠሩን ለእኔና ለሊቅ ዐዕቁ ተዉት።" ብለው ለሊቁ ከቀመሯቸው መወድሶች ሁለቱን እየተንተራደዱ ሰለቁት። ሊቅ ዐዕቁ በቅኔው ምሥጢር ተመስጠው ስቅስቅ ብለው አለቀሱ። ጉባኤው በዚሁ ታተመ። ቀብሩ በጠቢባን ወግ ተፈጸመ። ሐሽሣል የሚባለው የሊቁ ኖላዊ ግሩም መጽሐፍ በሊቅ ዐዕቁ እጅ ገባ። ድንቁም ታዖርያ በሚባለው በጠቢቡ ተዋነይ መጽሐፍ ደመና ጠቅሰው እንደሄዱ ደመና ጠቅሰው ከጎንደር ወደ ጎጃም ተመልሰው ከቅኔው ጎን ለጎን የጎንደርን ውኃ ምሥጢርና የተዋነይን ጥበብ ለፋሬስና ለሖረ እንዲሁም ለሦና አስተምረው ዐረፉ።

PDF Compressor Free Version

፪

ጎንጅ ደብረ ጥበብ-ገጸም

ሊቃውንት እያለቁ ዘመኑ እየከፋ ትውልድ እየጠፋ መጣ። ያች የሀገ

ሀብትኮ ለዚህ ትውልድ ፍቱን መድኃኒት ነበረች።" አሉ ፋሬስ።

"የትኛዋ?" አሉ ሐረ።

"አባታችን እንደ ዋሣ የነገሩን ያች ውኃ።"

"ዋትኛዋ የጎንደሯ ወይስ የዲማዋ?"

"የጎንደሯ እንጂ የዲማዋማ በነ-ሠረገላ ብርሃን ዘመን ታይታ ጠፍታለች።" አሉ ፋሬስ።

"የጎንደሯን ውኃ ማግኘቱ ከባድ ነው። ከቅርብ ቀን ወዲህ ብዙ ጠበብት ፈልገው አጥተዋታል። ጎንደር ውስጥ ብዙ የተቀበሩ አንቅዕት መኖራቸው ግልጥ ነው። ነገር ግን መላ-ጎንደርን ከገጠር አስተክተማ መርምሮ ውኃዋን ለማግኘት መለኮታዊ ተአምር ያስፈልግ ይመስለኛል?" አሉ ሐረ።

"ግድ የለም፣ ግድም የለም፣ እኛ የድርሻችንን እንወጣ። ከእንግዲህ ወዲህ የእኔና የአንተ ሥራ ውኃዋን በመፈለግ ላይ ቢሆን ይመረጣል። እንደ ዐሰትት ውኃ ለውኃ እየሄድን የድርሻችንን አንፈልግ። የቀለምና የጥበብ አባታችን ድንቁ ኩተዋነይ ጀምሮ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣውን ሀገራዊ ጥበብ ጠብቀው የድርሻቸውን አበርክተዋል።

ኖላዊ ዘጎንደርም ከዓመታት በፊት ለውኃዋ ለማዕት ሆነዋል። የዚህ ለማዕትነት እዳ-ከፋይ እኔና አንተ ነን። የሁሉን ጠቢባን ዓላማ

PDF Compressor Free Version

ማስቀመጫ ድንጋይ በጥበብ መውለድ ነው። አባት ልጁን በሥጋ ሲወልደው፣ ልጅ ደግሞ በፈንታው አባቱን ጥበብና ምሥጢር በመጠበቅ ይወልደዋል። እኔ ድንቁን ስወልድ አንተ ደግሞ የሕይወት ውኃን በማግኘት ስማዕቱ ኖላዊን ወልደህ ዓለምን ታስደምመው ይሆናል። ከዚች ቅጽበት ጀምሮ ሻሸህን ሳይሆን የምሥጢር ስንስለትህን ጠበቅ አድርግና ውኃዋን እንደምንም ለማግኘት ሞክር።" አሉ ፋሬስ ሁለቱ ሊቃውንት የቀለሙን ቀንድ ድንቁን ከቀበሩ ከብዙ ዓመታት በኋላ።

የጥበብ አባቷ ድንቁ በጎንጅ ደብረ-ዮበብ ሲኖሩ ቅኔ በማስተማርና ሀገራዊ ምሥጢር በመጠበቅ የተካኑ ነበሩ። ፋሬስና ሐረም ከድንቁ ቀለም ቀስመዋል። ከታብር በረከትም ተቋድሰዋል። በወሬ ወሬ የሰሚት የጎንደር ውኃ ግን በድንቁ ልብ ብቻ ቀርታለች። ድንቁ በሕይወት ላሉ "አልፎ አልፎ ጎንደር ስማር የጎንደርን ውኃ ጠጥቼ ቢሆን ኑሮ ይህንን ጊዜ ሞት ቀርቶ እርጅና አይነካካኝም ነበር።" ብለው ይጀምሩና መልስው ዝም ይላሉ።

በዚህ ጊዜ የቀለም ልጆቻቸው ፋሬስና ሐረ "በጎንደር የሞት መድኃኒት ውኃ አለች እንዴ?" ብለው ሲጠይቁ ድንቁ ፊት ይነሷቸዋል።

"አዎ! አባቶቻችን የጥንካሬ ጸጋ ነበራቸው። ከብረት ይጠነክራሉ። ከወርቅ ይጠራሉ። ሰብእናቸውም ጽኑእ ነበር። ጽናታቸውን ፈጣሪ ከሰጠን ዐለት ላይ አሻቦ ዘርተን ፍሬ እንዲያፈራ እናደርጋለን የሚል እምነት አለኝ።" አሉ ወጣቱ ሊቅ ፋሬስ።

"ነገሩን ቀለል አድርገው። እንደ ቂስ አደፍርስ ጥምጥም መደጉለል አያስፈልግም። ጥሬ ጨው መሸመት እንጂ አሻቦ መዝራት ድረስ

PDF Compressor Free Version

አያደርስም:: ... እያስተማርህ ይቺን ምሥጢራዊት ... ለመጭው ትውልድ ማድረስ አያቅትህም:: ለአብነት ተማሪዎች ... እያስተማርህ ቀለም እየነገርህ ትጠብቃታለህ::" ጠቢቡ ሖረ ወደ ... እየተመለከቱ ነገሩን ቀለል አድርገው ገለጹት::

"አንተስ?"

"እኔም እንደ ዐቅሜ "ስማዕቱ ኖላዊ" የሞተላትን ምንጭ እፈልጋለሁ:: በተለይ ይቺን ውኃ ከሰማዕቱ ኖላዊ እጅ ማን እንደተረከባት ባውቅ ፍለጋው ይቀልልኝ ነበር:: ግድ የለም:: እድሜ ዘመኔን እንደ ተጠማ ዋልያ ውኃ ስፈለግ እኖራለሁ::" ብለው ከልሙጡ ድንጋይ ላይ ተነሡ::

ከዚያም "በል አሁን እኔን በሰላም ሸኜኝ?" አሉ ጠቢቡ ሖረ ጥቂት ራመድ ራመድ እያሉ::

"ከእንዲህ ወዲህ ያችንን ውኃ ሳታገኝ ፊቴን አታየውም::" አሉ ወጣቱ ፋሬስ ሖረን እየሸኙ::

"እሱን ለኔ ተወው:: ዋናው ነገር አንተ እንደ ዐጤ ቴዎድሮስ ጀግና ሁን:: በታብር በኩል ከመጣ የሞት ጽዋ ከኔ ይለፍ ማለት የለብህም:: ቀስ ብዬ ስሰልልህ አልፎ አልፎ ወላዋዩ ቢጤ ነገር ነህ:: ውስጠ መሠሪነትህን ብዙ ሰዎች ስለማይረዱ በቀላል ነገር ሊደልሉህ ሊመጡ ይችላሉ:: ጥንቃቄ አድርግ:: በተለይ ተራዳኢ መልአክ መስሎ ከሚመጣ ሰይጣን ተጠንቀቅ::" ብለው ሖረ መንገድ ሲጀምሩ ፋሬስም ቆልማማ ከዘራቸውን እየተመረኮዙ ተከተሉ:: ከትልቁ ከተዋነይ ዋርካ ጀምረው ወደ ሰሜንመስዕ ጥቂት ተጉዘው ታብር በር ላይ ሲደርሱ "ስማቸውንና የመጽሐፉን ስም እንዳትረሳ አደራ:: የመጽሐፉ ስም ሐሸማል ነው::

PDF Compressor Free Version

ይህ[illegible] ይከው በጎንደር ውስጥ የሚኖሩት ምሥጢር አዋቂዉ ሊቅ ደግሞ ሊቅ ዐፅቁ ይባላሉ::" አሉ ሊቁ ፋሬስ ከዓመታት በፊት ድንቁ ቃል በቃል የነገሯቸው ስም ትዝ ብሏቸው::

"ጎንደር ስትደርስ ስማቸውን ጠይቅ:: የሚያውቅ ክሌላ በዐበቅ የለሽ ግደም ፈልጋቸው:: የድሮ ሰው ስለሆነ ከጠጂም ከመሽታዋም የወጉን ሳያደርሱ አይውሉም ሲባል ሰምቻለሁ መልካም መንገድ!! ሰፈራቸው እጨጌ ሰፈር ነው::" ብለው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ጠቢቡ ሖረ ወደ ፊት ገሠገሡ:: ሊቁ ፋሬስ እየቆዘሙ ወደ ተዋነይ ዋርካ ሲመለሱ የቅኔ ተማሪዎች ቅኔ ቆጥረው እየተመለሱ ነበር::

PDF Compressor Free Version

፫

ጎንደር

ጠቢቡ ሐረ ከፋራስ ተሰይተው ወደ ጎንደር ደርሰው በጨለማ ውስጥ ፊደላቱ ቀያይ ብርሃን የሚፈነጥቁ ሐሸማል የሚባለውን የጥበብ መጽሐፍ የያዙትን ሊቅ ዐፅቁን አግኝተው የሕይወትን ውኃ ለመቅመስ እንደ ቋመጡ ገጻቸው ያስታውቃል። ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ተነሥተው ጎንደር እስኪደርሱ ድረስ ይህንን ሐሳብ ሲያወጡ ሲያወርዱ መንገዱ ብዙ ቀን አልፈጀባቸውም ነበር። በተሰይ ሊቁ ፋራስ "ያችን ውኃ ሳትይዝ ፊቴን አታየውም። የመምህሩንና የመጽሐፉን ስም እንዳትረሳ" ያሉትን እያስታወሱ ሰነበቱ።

...ይህን ቃል እንደ ውዳሴ-ማርያም እየከለሱ፣ እየመለሱ፣ ከጎጃም ተነሥተው በአዲስ ዘመን በኩል አቋርጠው በሦስተኛው ቀን ጎንደር ገቡ። ጎንደር እንደ ደረሱ በደረታቸው ተንበልብለው የጎንደርን መሬት ሳሙ። ዐፈሩን ቃሙ። ከዚያም በውኃ ጥም የደረቀ ጉሮሯቸውን አርጥበው እግራቸውን አጥፈው እግረ-መንገዳቸውን የሊቅ ዐፅቁን ሰፈር ለመጠየቅ ከአንዲት በረንዳ ላይ ቁጭ ብለው ቡና ወደሚጠጡ ሰዎች ጉራ አሉ። ለራሳቸው በአካፋዳቸው ከያዙት ጥሬ ሽንብራ እየቆረጠሙ የእግዚርን ውኃ እየተጉነጨጩ ቀሪ ጉዳያቸውን ማሰላሰል ጀመሩ። በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ቀይ ብርሃን የሚያበራውንና ባሕር የሚያንድደውን የጥበብ መጽሐፍ እጅ ካደረጉ በኋላ በመጽሐፉ መሪነት ቀጣዩ ጉዞ ፍንትው ብሎ በአእምሯቸው መጣ። የምጥት ፊታቸው ፈካ።

PDF Compressor Free Version

"አሳጣውም" [illegible] ጮኽ ብለው:: ድካም ይጠይቃል እንጂ መጽሐፉ..." በረንዳ ላይ ክብ ሠርቶ ቡን የሚጠጣው ሰው ቀና ቀና እያለ ሲመለከታቸው ድንጋጤ ወረራቸው:: ወደ ጥሬዋ አቀረቀሩና በመዳፋቸው ቸርፍሰው ቃም ቃም አደረጉ:: ድፍርሱን ውኃ ጅ..ው..ው..አደረጉ:: በአትኩሮት ቀና እያለ የተመለከታቸው ሰው ወደ ቡናው አቀረቀረ:: መቀመጥ የሰለቸው ሒሳብ እየከፈለ ውልቅ አለ:: ጠቢቡ ሖረ እንደገና በውስጣቸው ማሰላሰል ያዙ::

"የመጀመሪያው ሥራዬ ሊቅ ዐፅቁን ፈልጎ ማግኘት:: ቀስ በቀስ መጽሐፉን በጥብቅ መመርመር:: ከዚያም በመጽሐፉ ምሥጢራዊ ቀይ ብርሃን እየተመራሁ የሕይወትን ውኃ ማሠሥ:: ያንን ሳገኝ ወደ ሁለተኛው ሥራዬ እገባለሁ...::" ይበልጥ ይኸኛው አእምሯቸውን ሰቅዞ ያዘው:: ወደ ጥበብ ዓለም በፍቅር ተስበው የገቡበትን ቀን መረቁ:: ቀና ብለው በጎንደር ሰማይ ላይ የሚውረገረገውን ደመና ተመለከቱ:: በደመና ተጭነው በኢትዮጵያ ሰማይ ሲንሳፈፉ በዐይነ-ሕሊናቸው ው..ል አለባቸው:: ይህንና ወደ ፊት ከሞት ተሰውረው የሚኖሩትን ምሥጢር ሲያስቡ ነፍሳቸው በፍሥሓ ያለ ጊዜዋ ቱ..ር..ር.. ብላ ልትወጣ ነበር:: ምኞት እንደ ስብ ተናንቋቸው መተንፈስ አቅቷቸው ገጻቸውን ሲያኮሳትሩ ጥሬዋ ሽንብራ ጉሮሯቸው ላይ ቁማ ላብ በላብ አደረገቻቸው::

ከዚያም ስመ-እግዚአብሔር ጠርተው ዐማትበው ከሐሳባቸው እንደ ምንም ባንነው ወደ ራሳቸው ሲመለሱ ፈገግ አሉ:: ከፊት ለፊት ቡን

PDF Compressor Free Version

እየጠጣ ነገረ-ሥራቸውን ሲመለከት የነበረ አንድ ፊተ-ቀጭን ሰው ጠ
ብሎ፤

"ይቅርታ መምሬ! ፈቃደኛ ከሆኑ ቡን ልጋብዝዎት አላቸው?"

"ተባረክ ልጀ!" አሉ ጠቢቡ ሖረ::

"ግድ የለም ልጋብዝዎት?::" ሰውዬው በትሕትና ተብሰከሰከ::

"ቡን ጋር ጠላት ነኝ:: ይቅርብኝ::" አሉ ጠቢቡ ሖረ ፈገግ ብለው::

"መጽሐፍ ቡና አትጠጡ ይላል?" አለ ሰውዬው አሮጌ መጽሐፍ በእጃቸው ይዘው ሲመለከታቸው ጊዜ ጥያቄው ድንገት መጥቶለት::

"መጽሐፉ እንኳን ጠጡም አትጠጡም ብሎ አይጥፍም:: ነገር ግን በታላላቅ ገዳማትና አድባራት ልዩ ሥርዐት መሠረት ቡን የሚጠጣ ዲያቆን ከቅዳሴ ይከለከላል:: እኔ ባደግሁበት ደብርም ካህን ቡን እንዲጠጣ አይፈቀድለትም:: ከጠጣ ከቤተ-መቅደስ ይባረራል::" አሉ ጠቢቡ ሖረ::

ጋባዡ መለስ ሲያጣ የራሱን ፍንጃል አንሥቶ ቡናውን ይጠጣ ጀመር:: ጠቢቡ ሖረም ያንን አሮጌ መጽሐፍ እያነበቡ ጥሬዋን ሽንብራ ሲቆረጥሙ ቆይተው::

"ይልቅስ ታውቅ ከሆነ ሊቅ ዐፅቁን ብታመለክትኝ በረከት ታገኛለህ?" አሉ::

ሰውዬው ጥቂት ሲያስብ ቆይቶ፤

"መሪጌታ ናቸው?" አለ::

"አዎ! ሊቅ መሪጌታ ናቸው:: ነገር ግን ጉባኤ ዘርግተው የሚያስተምሩ አይመስለኝም::" አሉ ጠቢቡ ሖረ

PDF Compressor Free Version

"ጎንደር ውስጥ ብዙ ሊቃውንት አሉ፡፡ በደንብ የሚታወቁ ጉባኤ-ቤት ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡ እስኪ ይቆዩኝ ላረጋግጥ፡፡" ብሎ፤

"ሊቀ መኳስ! ሊቀ መኳስ!" እያለ ሲጣራ በላዛ ጸጉሩ ላይ ሽበት የፈነጠቀበት ደልዳላ ሰውነት ያለው አዝማሪ መሰንቆውን እንደ ክላሽ አገንድሮ

"አቤት ጌታዬ ጨዋታ ፈለጉ?" አለ፡፡

"አይደለም! አይደለም! መቼም እናንተ አዝማሪዎች ከሥራችሁ ጋር የተየያዘ ስለሆነ በአብዛኛው የጎንደርን ነዋሪ ታውቃላችሁ፡፡ ከዚሁ ጎንደር ውስጥ ሊቅ ዐፅቁ የሚባሉ መምህር ካሉ ለእኒህ እንግዳ አባት ብታመለክታቸው በረከት ታገኛለህ?" አለ ሰውዬው ቡናውን እስከ ሥር ጨልጦ ፍንጃሏን ወደ ጠረጴዛው እየመለሰ፡፡

ሊቀ መኳስ መሰንቆውን ከትክሻው አውርዶ ጥቂት አሰብ አድርጎ፤

"ስማቸውን አላውቅም፡፡ ነገር ግን በበአታ ማርያም አካባቢ አንድ ቀጭን ሊቅ አሉ፡፡ እሳቸው ይመስሉኛል፡፡ አልፎ አልፎ ዐበቅ የለሽ እንገናኛለን፡፡ እኔ ስዘምር መምህሩ የወጉን ቀማምሰው መጽሐፍ በቃላቸው እያነበቡ ወደ በአታ ማርያም ይሄዳሉ፡፡ ለማንኛውም ወደ አባ ጃሌ ተክለ ሃይማኖት ሂደው ይጠይቁ፡፡" አለ ወደ አባጃሌ ዋርካ እየጠቆመ፡፡

ጠቢቡ ሖረ ሁለቱንም አመስግነው ወደ አባ ጃሌ ዋርካ በረሩ፡፡ የተቀበረውን የአበውን ጥበብ ከመቃብር ለማንሣት፡፡ ጥበቡ ሳይፈርስ ምሥጢሩ ሳይበሰብስ በነፍሱ ለመድረስ ተራወጡ፡፡

PDF Compressor Free Version

ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ከተዋነይ በኋላ ተዋነይን የሚተካ የቀለምና የጥበባ
ሊቅ ለማግኘት ብዙ ዘመናትን አሳልፋ ነበር። ከዘመናት በኋላ ድንቁ
ተተኩ። ድንቁ ሲሞቱ ግን ድንቁን የሚተካ ሊቅ ማግኘት እንደዘበት
ሆኖባቸው ነበር-ካህናቱ። ከበዙ ጭቅጭቅ በኋላ በሊቃውንቱ ምርጫ
ባለቅኔው ፋሪስ ተተኩ። በመጀመሪያው ቀን በድንቁ የቅኔ ዙፋን
ሲሰየሙ በቀለም አየያዛቸው አባታቸው ድንቁን መሰሉ። ጠምም
ጀማምሯቸዋል። ከዘራ ወያያዛቸውም ሆነ ቀለም አነጋገራቸው ቁልቂ
ድንቁን ሆነ። በተለይ መወድስ ሲዘርፉ ከድንቁ ላቅ ብለው እንደተዋነይ
ፊለክ-ፊለካት ድረስ ሂደው በሥነ-ፍጥረት ምሥጢር ላይ አጠነጠኑ። ያ
ብቻ አይደለም። ባንዲት ምሽትም ከዐሥር በላይ መወድሶችን ሲሰልቁት
የጎንጅ ደብረ-ጥበብ ካህናት ተደመሙ። አነዘልባል ጋር የተከራከሩበት
የመጀመሪያው ቅኔ ደግሞ እነሆ ይህን ይመስል ነበር። በአንድ የቅኔ
ምሽት ሊቁ ፋሪስ በቅኔ ዙፋኑ ሲሰየሙ ወፈ ሰማያት ተማሪዎች በሊቁ
ዙሪያ ተኮለኮሉ። ነዘልባል የሚባል የቅኔ ዘራፊ ከተማሪዎች መኻል
በሊቅነቱ ጎልቶ ታየ። ሊቁ ፋሪስ በነፋስ ፍጥነት፦

"ጠቢባን አበው ዘጥበቦሙ ሐዲስ
ፈረሶሙ ኮነ ደመና ወመንኰራኵሮሙ ጢስ።" ብለው አጭር ቅኔ ዘረፉ።
ወደ አማርኛ ሲተረጎም ደግሞ፦

"የቀደሙ አባቶች ጥበባቸው ሐዲስ፣
በቅሏቸው ደመና ሩቢላቸው ጢስ፣
አዳሜ ይሮጣል ኮኖላቸው ላይደርስ።" የሚል ነበር።

PDF Compressor Free Version

"ቅኔ ዘራፊ ሲኾን ስለሚል የሚባለው የቅኔ ዘራፊ "የኔታ! ቅኔው ይበል ነው! እንደ አባትም እንደ ድንቁ ቀሰሙን እንደ ወረደ የያዙት ይመስለኛል። የቅኔው አጠባል ማርኮኛል። ጉባኤ ቃናም እንዲህ ከሰላ ረጅሙ መወድስ ምን ያኽል እንደሚመስጥ ጉባኤ-ቃና ከሚባለው ቅኔም ተረድቻለሁ። ነገር ግን ስምና ወርቁ ከተፈጥሮም ሆነ ከሰው ልጅ የኑሮ ዘይቤ ወጣ ያለ ይመስለኛል?" አለ ነበልባል በትሕትና።

"እንዴት?" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"በተፈጥሮ ምሥጢር ስንመራ ደመናውን እንደበትሉ ፍጡር ሊጋልበው? ጢሱን እንደሮቢላ ጠቢባን ሊሳፈሩበት እንዴት ይችላል? ይህ ስምና ወርቅ ቅኔ ለዚህ ዘመን ትውልድ ምትሐት እንጂ አማናዊ ሥራ አይመስልም።" ነበልባል በውዳሴ ጀምሮ ወደትችት ተንደረደረ።

"የደመናውን ምሥጢር እየቆየን እንመራመርበታለን። ለጊዜው ቅኔው ብቻ በቂ ነው። እንደ ቅኔ ተማሪነትህ መወድሱ ላይ ተፈላሰፍ። የሥነ-ፍጥረትን ምሥጢር እኛ ልጆች ቀርቶ ጠቢባን አባቶቻችንም ጀመሩት እንጂ አልፈጸሙትም። በእርግጥ ለዚህ ትውልድ ስምና ወርቁ እንቆቅልሽ ነው" የሚለው ሐሳብ በእኔ ውስጥም አለ። ወደ እውነታው ስንመጣ ግን ብረት አቅልጦ በደመናው ላይ ከመጋለብ ይልቅ ራሱን ደመናውን መጋለብ ይሻላል ባዩ ነኝ። እንዲያውም የቅኔው ፈላስፋ ተዋነይ ይህንን ምሥጢር ሞክሮት ነበር ይባላል። የትንጅ ደብረ-ጥበብ ሊቃውንት እንደሚነግሩን ከሆነ ደግሞ በክፉል የተሳካለት ይመስለኛል። ዛሬ ግን የተዋነይ ጥበብ ቀርቶ ራሱ ተዋነይ አፈ-ታሪክ እየሆነ መጥቷል። ደራስያን ሳይቀር በቅኔ ቤት አፈ-ታሪክ "ተዋነይ ለባት

PDF Compressor Free Version

፬

ሳንጅ ደብረ-ጥበብ ከተዋነይ በኋላ ተዋነይን የሚተካ የቀለምና የጥበብ ሊቅ ለማግኘት ብዙ ዘመናትን አሳልፋ ነበር። ከዘመናት በኋላ ድንቄ ተተኩ። ድንቁ ሲሞቱ ግን ድንቁን የሚተካ ሊቅ ማግኘት እንደጠበቁት ሆኖባቸው ነበር-ካህናቱ። ከብዙ ሟቅጭቅ በኋላ በለቃውንቱ ምርጫ ባለቅኔው ፋሬስ ተተኩ። በመጀመሪያው ቀን በድንቁ የቅኔ ዙፋን ሲሰየሙ በቀለም አየያዛቸው አባታቸው ድንቁን መሰሉ። ጢምም ጀማምሯቸዋል። ከዘራ ዐያያዛቸውም ሆነ ቀለም አንጋገራቸው ቁልጭ ድንቁን ሆነ። በተሰይ መወድስ ሲዘርፉ ከድንቁ ላቅ ብለው እንደተዋነይ ፊስኩ-ፊስካት ድረስ ሂደው በሥነ-ፍጥረት ምሥጢር ላይ አጠነጠኑ። ያ ብቻ አይደለም። ባንዲት ምሽትም ከዐሥር በላይ መወድሶችን ሲሰልቁት የሳንጅ ደብረ-ጥበብ ካህናት ተደመሙ። አነበልባል ጋር የተከራከሩበት የመጀመሪያው ቅኔ ደግሞ እነሆ ይህን ይመስል ነበር። በአንድ የቅኔ ምሽት ሊቁ ፋሬስ በቅኔ ዙፋኑ ሲሰየሙ ወሬ ሰማያት ተማሪዎች በሊቁ ዙሪያ ተኮለኮሉ። ነበልባል የሚባል የቅኔ ዘራፊ ከተማሪዎች መኻል በሊቅነቱ ጎልቶ ታየ። ሊቁ ፋሬስ በነሩስ ፍጥነት፦

"ጠቢባን አበው ዘጥበቦሙ ሐዲስ
ፈረሶሙ ኮነ ደመና ወመንኰራኵሮሙ ጢስ።" ብለው አጭር ቅኔ ዘረፉ።

ወደ አማርኛ ሲተረጎም ደግሞ፦

"የቀደሙ አባቶች ጥበባቸው ሐዲስ፣
በቅሏቸው ደመና ሩቢላቸው ጢስ፣
አዳሜ ይሮጣል ኮኖላቸው ላይደርስ።" የሚል ነበር።

"ቅኔ ዘረፋው በኂላ ነበልባል የሚባለው የቅኔ ዘራፊ "የኔታ! ቅኔው ይበል ነው! እንደ አባትው እንደ ድንቁ ቀለሙን እንደ ወረደ የያዙት ይመስለኛል:: የቅኔው አጠጣል ማርኮኛል:: ጉባኤ ቃናዎ እንዲህ ከሰላ ረጅሙ መወድስ ምን ያኽል እንደሚመስጥ ጉባኤ-ቃና ከሚባለው ቅኔዎ ተረድቻለሁ:: ነገር ግን ሰምና ወርቁ ከተፈጥሮም ሆነ ከሰው ልጅ የኑሮ ዘይቤ ወጣ ያለ ይመስለኛል?" አለ ነበልባል በትሕትና::

"እንዴት?" አሉ ሊቁ ፋሬስ::

"በተፈጥሮ ምሥጢር ስንመራ ደመናውን እንደበቅሎ ፍጡር ሊጋልበው? ጢሱን እንደሮቢላ ጠቢባን ሊሳፈሩበት እንዴት ይችላል? ይህ ሰምና ወርቅ ቅኔ ለዚህ ዘመን ትውልድ ምትሐት እንጂ አማናዊ ሥራ አይመስልም::" ነበልባል በውዳሴ ጀምሮ ወደትችት ተንደረደረ::

"የደመናውን ምሥጢር እየቆየን እንመራመርበታለን:: ለጊዜው ቅኔው ብቻ በቂ ነው:: እንደ ቅኔ ተማሪነትህ መወድሱ ላይ ተፈላሰፍ:: የሥነ-ፍጥረትን ምሥጢር እኛ ልጆች ቀርቶ ጠቢባን አባቶቻችንም ጀመሩት እንጂ አልፈጸሙትም:: በእርግጥ ለዚህ ትውልድ ሰምና ወርቁ እንቆቅልሽ ነው" የሚለው ሐሳብ በእኔ ውስጥም አለ:: ወደ እውነታው ስንመጣ ግን ብረት አቅልጦ በደመናው ላይ ከመጋለብ ይልቅ ራሱን ደመናውን መጋለብ ይሻላል ባዩ ነኝ:: እንዲያውም የቅኔው ፈላስፋ ተዋነይ ይህንን ምሥጢር ሞክሮት ነበር ይባላል:: የጎንጅ ደብረ-ጥበብ ሊቃውንት እንደሚነግሩን ከሆነ ደግሞ በከፊል የተሳካለት ይመስለኛል:: ዛሬ ግን የተዋነይ ጥበብ ቀርቶ ራሱ ተዋነይ አፈ-ታሪክ እየሆነ መጥቷል:: ደራስያን ሳይቀር በቅኔ ቤት አፈ-ታሪክ "ተዋነይ ሰባት

PDF Compressor Free Version

ዓመት መልአክ ሞትን የገዙተ ሊቅ ነበር" እያሉ የነበረውን እንዳልነ
PDF Compressor Free Version
አድርገው ሲከትቡ ይታያሉ:: እሱን ገልጠን ማስተማሩ የ
የሊቃውንቱ ድርሻ ነው::" አሉ ሊቁ ፋሬስ::

"የቅኔውን ሰምና ወርቅ ግን አማናዊ አድርገን መውሰድ እንችላለን?" ነ
ነበልባል::

"እንወስደዋለን!::" ፋሬስ ራሳቸውን ባንቱታ አንቆለጳጳሱ::

ሊቁ ፋሬስ የእድሜያአቸውን ግማሽ የጨረሱት በቅኔ ትምህርት ነው:: ደብረ-ቢዘን፣አክሱም ጽዮን፣ ቤተ-ቀጢን፣ ዋድላ ደላንታ፣ ጎንደር ገለዓ ቅኔ ቤት፣ደብረ ምእራፍ ዋሽራ ማርያም፣ ዲማ ጊዮርጊስ፣ በሸዋም ደብ ብርሃን ሥላሴ፣አንኮበር ሥሬ መድኃኔ ዓለም፣ አዲስ ዓለም ገዳ ሌሎችም ዛሬ በከፊል የጠፉ የቅኔ ትምህርት ቤቶች የሊቁ የፋሬ የቀለም ሀገራት ነበሩ:: ከእኒህ ቅኔ ቤቶች ሲማሩ አድገው በመጨረሻ በጎጃም ክፍለ-ሀገር ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ከተዋነይ ቅኔ ቤት ትምህርታቸውን አሣረጉ:: የጎንጁ ሊቅ ድንቁም ከቀለሙ ጎን ለጎ የታብርን ምሥጢር መረቋቸው:: ሊቁ ፋሬስ የምሥጢር ሰው ሆኑ::

ነበልባልም ቢሆን ቀላል ተማሪ አይደለም:: በዐራቱ ማእዘን ዞሮ ቀለም በማጥናት ደክሟል:: 'የሺ ፍልጥ ማሠሪያ ልጥ' ነውና እስካሁን የሰበሰበውን የሚያሥርበት ሐረግ ለመሳብ ጎንጅ ደብረ-ጥበብን ተቀላቀለ:: ልቦናው ከታብር ለመቋደስ ፈለገ:: ጎንጅ ሲደርስ ግን በቀለም አያያዛቸው ፋና-ወጊው ሊቅ ድንቁ አልፈው ፋሬስ በቅኔ ዙፋናቸው ተተክተው አገኘ::

PDF Compressor Free Version

ድንቁን በአካል ቢያጣቸውም ቀለማቸው በፋራስ ልብ ተጽፎ፣ መወድሱ ደምቆ ተቀበለው። "መጠኑ ሰረድዕ ከመ ሊቁ" የደቀመዝሙር መጠኑ እንደ መምህሩ ቢሆን ነው የሚባለው ቃለ-መንገል በፋራስና በሐረ የልብ ጽላት ተጽፎ ነበር።

ክርክሩ ቀጠለ።

"የኔታ ቅኔው በደንብ አልገባኝም። በደንብ መረዳት እፈልጋለሁ?"

"ምኑ ነው ያልገባህ?" አሉ ሊቁ ፋራስ።

"ሰምና ወርቁ?"

"ቅኔው በሰምና በወርቅ ላይ ብቻ የተቀነበበ አይደለም። ቅኔው የሚገልጠው ሌላ አዲስ ምሥጢርም አለው። ያንን ደግሞ እየቆየህ ትደርስበታለህ።" አሉ ፋራስ።

"ዛሬ ቃል በቃል ጠይቁ ነልገባኝ ሌላ ጊዜ እንዴት ልደርስበት እችላለሁ?" ነበልባል ወደፊት የሚደርስበት ቅኔ ብቻ መስሎት በጥያቄ ትንፋሽ ነሣቸው።

ሊቁ ማብራራት ቀጠሉ።

"የቅኔ መንገዶች በመቶ የሚቆጠሩ ሲሆኑ ጥቂቶቹን ብቻ ብናነሣ እንኳን አውታረ-ፊደል፣ ሥራና፣ ዐይነ ውኃና ምርምር ቅኔ በመባል ይታወቃሉ። እኒህም የሃይማኖት የታሪክ የባሕል የፍልስፍና ምንጮች ናቸው። በተለይ ፍልስፍና-ነክ ቅኔዎች ለምርምር ይጠቅማሉ። ከሃይማኖት አስተምህሮው ወጣ ብለው በታሪክ በዕፀዋትና በጥበብ ላይ የሚያጠነጥኑ መወድሶች የጠቢባኑ የጥበብ ማኅተም ተቀርጸባቸው እናገኛለን።" አሉ ሊቁ ፋራስ።

PDF Compressor Free Version

"ታዲያ ይህ ቅኔ ከማንኛው መንገድ ይመደባል? ዐይነ-ውኃ መንገድ ወይስ ምርምር ሰምና ወርቱ ምን ይባላል?" አለ ነበልባል።

"ቅኔው ምርምር ወይም ፍልስፍና አይደለም። ከተለመደው የቅኔ መንገድ ወጣ ያለ ነው። ዝአንበ ዴዴሃ ይበልዕ ፍራሃ አንዳሉ አበው ፍራንገሩ ወደፊት በዐይን የሚታይ ይሆናል።" ብለው ወደ ዕለቱ ጉባኤ ገቡ። አንዱን ወጣኒ ተማሪ "ና- ወዲህ ልጄ!" ብለው የቆጠረውን ቅኔ ሰምተው ለማስተካከል ጀራቸውን ወደ ወጣኒው ተማሪ ዘንበል አድርገው ማዳመጥ ጀመሩ።

ነበልባል "እንዲያ ይበሉኝማ! እሰይ የኔ ባለ ቅኔ! ወደ ፊትማ እኔም ብዙ እጠብቃለሁ። በቅሏቸው ደመና ሊሆን እንዴት ቻለ? ሮቢላቸው ጤሰ? ደግሞ ጠዚባን? የጦበብ ሊቃውንቱ እንማን ይሆኑ?" እያለ በውስጡ ሲያወጣ ሲያወርድ ከናፍሮቹ እየተወራጩ ነበር።

PDF Compressor Free Version

፫

ጎንደር-እጨጌ ሰፈር

ጠቢቡ ሐረ ሰዓቱ ለዐይን ያዝ ሊያደርግ ከእጨጌ ሰፈር ደረሱ። አካባቢው ጭር ብሏል። በእቅዳቸው መሠረት ስለ ሕይወት ውጋና ስለ ጎንደር ምሥጢር ያውቃሉ ብለው የቀለምና የጥበብ መምህራቸው አለቃ ድንቁ የነገሯቸውን ሊቅ ዐፅቁንና ሐሸማል የሚባለውን ባሕሩን እንደ ቤንዚን የሚያነድ መጽሐፍ ይኖርበታል ተብሎ ወደሚገመተው ሊቅ ዐፅቁ ቤት ለመሄድ ነበር።

ቀን ቀን ጠጅ በመሸጥ የሚታወቁት የእጨጌ ሰፈር ቤቶች ምሽቱን ተከትለው እንደ ወጉ ተዘጋግተዋል። የጠጁ መዓዛ አልፎ አልፎ ያውዳል። ጠቢቡ ሐረ ግራ ቀኙን የእጨጌ ሰፈር በከፊል እየገላመጡ ወደ እጨጌ ሰፈር ከደረሱ በኋላ በትትክል መጽሐፉና ሊቁ ይኖሩበታል ተብሎ የሚገመተው ከእጨጌ ቤቶች ውስጥ ደርብና ምድር ቤት ያለው ዋናው ቤት ግር አላቸው። ቤቱን ለማረጋገጥ ለምልክት በሥዕለ አድኅኖ መልክ የያዙትን ከተጠረበ ድንጋይ ላይ የተሳለ ሥዕል ከአክፋዳቸው አወጡ። በጠቢባኑ አባቶች እጅ የተሣለው የቤቱ ምስል ደርብ አለው። ከዚኽኛው ጋር በቅርፅም በደርብም አይገናኙም። በዚህ መሠረት ደርብ በደርብ የተሠሩ ብሉየ-መዋዕል ቤቶችን እየመረጡ ይመለከቱ ጀመር። በመጀመሪያ ከአንድ ብሉየ-መዋዕል ቤት ጋር ተጋጠሙ። ቤቱ ደርብ ቢኖረውም የደርቡ መወጣጫ የተሠራው በእንጨት መሰላል ነው።

"አይደለም አይደለም! ይህ አይደለም!" ብለው አሰቡት።

PDF Compressor Free Version

ቀጥሎ ዝኒጋባ መሳይ ካለው ቤት ደረሱ። ልባቸው ሲአድለው ድንጋ
ከያዙት ሥዕል ጋር አመሳስሉት። አልተመሳሰለላቸውም። ቤቱ ላይ
የመጽሐፍ ቅርፅ የለውም። ሦስተኛውን ቤት ሲፈትሹ ላዩ ደርቧ
ደርቧ መሰላሉ የድንጋይ መውጫ የሆነ ቤት ጋር ተፋጠጡ። መሬ
መድረኩ ላይ የመጽሐፍ ሥዕል መኖሩን ተመለከቱ። በከፊል ትክክ
ነበሩ። ቤቱ መብራት የሌለው በርባሮስ የወረረው ፍሌማ ነው። ከያዙት
ሥዕል ጋር ሲያመሳስሉት ሃያ ግጥም አለ። የተጠረበውን መልመሌ
ድንጋይ ወደ አካፋዳቸው መልሰው ወደ ውስጥ ተመለከቱ። በሰንሰለ
ተጠርቅሟል። የሰንሰለቱን ሕብለ-ሰረሰር ተከትለው ወደውስጥ ቢመለከቱ
የውስጠኛው የቤቱ በርም ተቆልፏል። በዚያውም ላይ ቤቱ ኑብድቢድ
ብሏል። ዘወር ዘወር እያሉ አካባቢውን መቃኘት ጀመሩ። ድምፅ የለም።
"ወይኔ ሐረ!" አሉ ጠቢቡ ሐረ ከቤቱ ጋር የመጽሐፉ መከርቸም
አሳዝኗቸው። ያ ታሪካዊ መጽሐፍ በአእምሯቸው ብልጭ ብሎባቸው።
"ወይኔ ጎንደር! ወይኔ ፋሲል! ወይኔ! ወይኔ ሀገሬ! ወይኔ የጎንደር
ክዋክብት!" አሉ ቀደም ብለው ያለፉ የጎንደርን ሊቃውንት አንድ ባንድ
በውስጣቸው አስበው።

ከዚያም የገቢውን በር እንደ ብረት በጠነከረ እጃቸው መደብደብ ሲጀምሩ
"ማን ነህ? እድ ወደላይ?" አለ አንድ ጎርነንያለ ድምፅ።

ጠቢቡ ሐረ ክው አሉ። "ፈትህን አዘር!" አለ በድጋሚ

ሐረ ሰማይ ጨለመባቸው። ሌሊት ሌሊት ቀይ ብርሃን እየተፋ በፍሌማ
የሚነበበው መጽሐፍ ጨለማ ለበሰላቸው። የነ-አውግቸው መጽሐፍ ወማ
ብቻ ሆነባቸው።

PDF Compressor Free Version

ጥበቃው ማንደፍሮ በሩን አንኳኩቶ ሲወጣ ጠቢቡ ሐረ ገጻቸው ጠቁሮ በሩ ላይ ተንተረዋል።

"እጅ ወደ ላይ?" አለ ጥበቃው ማንደፍሮ ጠብመንጃውን ወደ ሐረ ደግኖ።

"ጤና ይስጥልኝ?" አሉ ጠቢቡ ሐረ ወደ መሬት ሸብረክ ብለው ደረታቸው ዐፈር እስኪነካ ድረስ ሰግደው ጠቡን ለማቀዝቀዝ።

"እጅ ወደ ላይ ብቻ!። ስግደትህን ለእግዜር፣ እጅህን ለመንግሥት ስጥ። እኔ እጅህን እንድትሰጥ ነው የምፈልገው።" አለ ማንደፍሮ።

"ጌታዬ ይቀርታ!" እኔ ለነፍሴ ያደርሁ ሙት መነኩሴ ነኝ። መነኩሴ ማለት 'ዘሞት እምዓለም' ማለት ነው። ብትገድለኝም አይቆጨኝም። ቀድሞ መቻለሁ።" ብለው እጃቸውን እንደ ጭራሮ አንከረፈፉ።

ማንደፍሮ ጥቂት ተረጋግቶ "ታዲያ መለኩሴ ከሆኑ በዚህ ጨለማ ምን አመጣዎት?" አለ ጠብ መንጃውን ከሐረ አቅጣጫ እየመለሰ።

"አመጣጤ ታሪክ ነጋሪ አፈ-ሊቅ መኖራቸውን ሰምቼ፣ ታሪክ ላጠና ነበር። እንዲያውም ከቻልህ ከአባታችን ጋር ብታገናኘኝ?"

"ማንደፍሮ ሐረን ገላምጦ ጥቂት ከተመለከተ በኋላ

"አልሰመም ነው ጌታዬ?" አለ በከፊል ቀዝቅዞ።

"ምኑን?" አሉ ጠቢቡ ሐረ ልባቸው ከሁለት ስንጥቅ ብሎ።

"ጀርመን ሀገር እንደ ሄዱ ወደ ሰማይ ቤት መሄዳቸውን!።"

ጠቢቡ ሐረ ሊቅ ዐፅቁ ያረፉ መስሏቸው መናገር ቀርቶ መተንፈስ ተሳናቸው። መጽሐፉም ዝም ቄሱ ሐረም ዝም። እንደ ቆመ ላብ ሲውጣቸው።

PDF Compressor Free Version

"አይዞዎት ጌታዬ አይዞዎት! አይደንግጡ! ወደ ማይቀርበት ዓለም መሄዳቸው ለእሳቸው ፍሥሐ ነው። የቀሩብን ለእኛ ብቻ ነው። ለዚች ደሃ ሀገር የረባ ውለታ ሳይውሉ መሄዳቸው እንጂ የሚያስቆረቁረው ለሊቁ ዕረፍት ነው። ከጀርመን የተመለሰው በድናቸው ነው።" አሳ ማንደፍሮ።

ከዚያም ወደውስጥ አስገብቶ እስኪረጋጉ ድረስ አረፍ እንዲሉ አደረጋቸው። ጥቂት እንዳረፉ ውኃ አምጥቶ ፊታቸውን እንዲታጠቡ ካደረገ በኋላ ወግ ጀመሩ።

"ለመሆኑ መቼ አረፉ?" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"እንትና እንት ዘመን አለፋቸው"

"እርስዎ የቤቱ ወራሲ ነዎት?"

"አይደለሁም! ጥበቃ ነኝ።

"ሊያርፉ ቤቱን ማን ተረክበው ጌታዬ!።" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"ስጊዜው የተረከበው መንግሥት ነበር። አሁን ግን ቤቱ ተሸጧል።" አለ ማንደፍሮ።

"ማ..ማን ሸጠው?" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"መንግሥት ተረክቦ ሳይውል ሳያድር በሃራጅ ሸጠው።" አለ ማንደፍሮ ጠብ-መንጃውን ወድሮ በጥልቀት እያጤናቸው።

"ማ...ማ..ን... ገዛዉ?" ጠቢቡ ሐረ እንደበታቸው እየተሳሰረ ጠየቁ።

"በቅርቡ ግእዝ ለማስተማር ጎንደር የነባ ጀርማናዊ ባዕሉ-ጸጋ ነው አሉ።"

PDF Compressor Free Version

"...ጀ...ጀ...ጀ...ጀርመናዊ ፍቅር ያለህ! ጀርመናዊ በዚያውም ባለጸጋ! የፊጣሪ ያለህ!::" እያሉ በውስጣቸው ሲናደዱ ድጋሚ ላብ ዘፊቃቸው:: ማንደፍሮ ሁኔታቸውን ሲያጤን ቆይቶ ከሰውዬው ሞት የቤቱ መሸጥ ለምን ላብ በላብ እንዳደረጋቸው አልገለጥለት ሲል፣

"ይበሉ! ይነሡ ጌታዬ! ጊዜው እየመሸ ነው:: ወደ ማደሪያዎ ይሄዱ:: ዘንድሮ ይህ ቤት ጣጣ እያመጣ ነው:: ጣጣው እንደ ይተርፍም ቀሰ ብለው ይውጡ::" አለ::

"የምን ጣጣ ልጀ?" አሉ ጠቢቡ ሐረ::

"ይህ ቤት ድሮ የእጨጌዎች ማረፊያ ብቻ ነበር ይባላል:: እጨጌዎች ሲያርፉ ቀስ በቀስ የጎንደር ፊላስፎች እየተፊራረቁ መጽሐፍ ሲያነቡበት ይኖሩ ነበርም ይባላል:: ፍሬ ፍሬ የሆኑ የጎንደር ሊቃውንትም ቤተ-መክራ አድርገው ተጠቅመውበታል:: ከባለ ቅኔው ክፍለ ዮሐንስ ጀምሮ ሊቃውንቱ በዚህ ስፍራ ተፊላስፊውበታል:: ከሊቃውንቱ አንዱ ሰማዕቱ ኖላዊ ይባሉ ነበር:: ሰማዕቱ ኖላዊ እጨጌ ሆነው በዚህ ስፍራ ሲኖሩ ወደ ጀርመን ሀገር ግእዝ ለማስተማር ሄዱ:: ቅዱስ የሆነውን የግእዝ ቋንቋ እያስተማሩ እስኪሞቱ ድረስ ይህንን ቤት ሲናፍቁ ነበር እያሉ ሲያወሩ እሰማለሁ:: እሳቸው ሲያርፉ ቤቱ "ቤተ መዘክር" ሆኖ በቅርስነት ይመዘጋባል ሲባል መንግሥት ተረክቦ ጨረታ አወጣበት:: ይህንን የሰሙ የጎንደር ሊቃውንት እያጉረመረሙ ነው::" አለ ማንደፍሮ::

"የሊቃውንቱ ጉርምርታ ምኑ ላይ ነው?" ጠቢቡ ሐረ የማንደፍሮን እውቀት ለመሰለል ምንም የማያውቁ መስለው ተፊላስፉበት::

PDF Compressor Free Version

"ግልጥ አይደለም አባቴ። አንዳንዶቹ ቤቱ በድሮ ዘመን አጨናንቆን የተለያዩ ምሥጢራትን ይፈኖመብት ነበር። በዚያም ላይ የተቀበረ መጽሐፍ አለ እያሉ ያሟርታሉ። መጽሐፉ ደግሞ ያለ ሩና በጨለማ የሚነበብ ድንቅ ብርሃን ያለው መጽሐፍ ነውም ይላሉ። የጠቡ መንሥኤ ያ ነው። በዚህ ሰሞን ጠቡን እንደ ሰደድ-እሳት የቆሰቆሱት ግን የቅኔ ተማሪዎችና የብልኮ ሰፈር አዝማሪዎች ናቸው። አዝማሪዎች በመሰንቆ መጽሐፉን የሚያሞግስ ግጥም እየገጠሙ ሲሸልሉ የቅኔ ቤት ተማሪዎችን ደግሞ የቅኔ መዘራረፊያ አድርገውታል ይባላል። ይህንን የሰማ ጎንደሬ አውነታው ይውጣ እያለ በመንግሥት ላይ ጦር እየመዘዘ ነው።"

ከዚያም ወደ ራሱ የሥራ ድርሻ ተመልሶ አከለበት። "ለእኔ ግን ይህ ሁላ ታሪክ ምንም አይደል። እኔ የማውቀው ጀመርናዊዉን ጌታዬን ብቻ ነው። ጡበቅ ብሎ ደመወዝ እስክከፈለኝ ድረስ እጠብቃለሁ። ታሪኬ እሱ ነው። ታሪኩን የጎንደር ሊቃውንት ይናገዱበት። ይፋጩበት። ይናጨበት። ለእኔ ምኔም አይደል። ሥራዬ ተግቶ ቤቱን መጠበቅ ብቻ ነው። እጠብቃለሁ።"

ጠቢቡ ሐረ በብሽቀት ሲመለከቱት ቆይተው፤

"ጠቡን የእንተ ጥበቡን የኔ ይበለው።" አሉ በውስጣቸው።

ከዚያም "ጀርመናዊዉ ቤቱን መቼ ይረከባዋል? ቀን ተቆርጦለታል?" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"ባለፈው ወር ቤቱን ሊረከብ መጥቶ ነበር። ግርግር ሲነሣበት በሚመጣው ወር ሊረከበው ተስማምቶ ሄደ።" አለ ማንደፍሮ።

PDF Compressor Free Version

"በማመጣው ወር ግርማ መፍትሔ ያገኝ ይመስልኻል?" ጠቢቡ ሐረ በተአምርም ቢሆን ጣልቃ ገብተው መጽሐፉን እጅ ለማድረግ አውጠነጠኑ።

"ግርማሩ እንኳ በንግግርም ሆነ በሠራዊት ታይል የሚፈታ አይመስለኝም። እንዲያውም ሰሞኑን ከባድ ጠብ ሳይነሣ የማቀር አይመስለኝም።" አለ ማንደፍሮ የጠቢ-መንጃውን አንገት በጣቶቹ እየነካካ።

"እንዴት..አወቅህ?" አሉ ጠቢቡ ሐረ በማርሻር ከጀመርናዊ እጅ ቤቱ ሲተርፍ ታያቸው።

"በሕልሜ ታይቶኛል።"

"እንዴት ታየህ?" አሉ ፍንጭት ጥርሳቸውን ፈገግ አድርገው።

"በሕልሜ የጠብ መንጃዬን አፈሙዝ ደም ስቀባ አድራአለሁ። ይሆን ሕልም ሌላም ጊዜ በሌላ ሰው ላይ አይቼው አውቃለሁ። ያ ሰው ዛሬ የለም። ተታኩሶ ሠውቶ ተሠውቷል። ይህንን ሕልም ከአየሁ ወዲህ እኔም ጥንቃቄ እያበዛሁ እገኛለሁ። እርስዎም ከሞት የተረፉት በወስድሁት ከባድ ጥንቃቄ ነው። ፈጥኜ እንደ ብረት ድስት ሽሮ የቀዘቀዝሁት። ምላጩን እንደ ረገጥሁ ያ ግም ሕልም ትዝ ብሎኝ ነው። ምላጩን እንደ ጨበጥሁ ስቤው ቢሆን ኑሮ የሕልሙ ፍቺ ርስዎ ነበሩ። አሁንም ቢሆን ፈቅ ይበሉ። ባልሳሳት መነሱሴ ይመስሉኛል። የጠቡ ተቋዳሽ እንዳይሆኑ ወደዚህ ስፍራ ባይመጡ ይሻላል።" ብሎ ወደ ውጪ ይሂዋቸው ወጣ። ቤቱን በደንብ ሊመለከቱ ሲሉ ወደ ፊት ገፍትሮ በሩን ከረቸመባቸው።

PDF Compressor Free Version

፯

ሊቁ ፋሬስ ጠቢባን አበው ብለው ጀምረው ስለ ጠቢባን ቅኔ በዚሩ በነጋታው በምሥጢር በሰል በሰል ያሉ ተማሪዎች ሊቁን ዙሪያ ጥምጥም አብበው ወጣ ወጣ ያሉ ጥያቄዎች ማንሣት ጀመሩ።

"የኔታ አለ?" አንድ ረሐብ ያደቀቀው ቀጫጫ ተማሪ።

"አቤት!" አሉ ሊቁ ፋሬስ በትሕትና።

"ተዋነይ በደመና እየተጫነ ዓለምን ይዞር ነበር የሚባለው እውነት ነው?" አለ ናርሐት እያራደጡ።

"እንደሱ ያለው ማን ነው?" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ከአፈ-ታሪክ ሰምቼ ነው" አለ ያ ቀጭን ተማሪ እንደ ገመድ በቀጠነ አንገቱ ራሱን እያወዛወዘ።

"ወሸከሬ!" አሉ ሊቁ በመደመም።

"ወሸከሬ ሁላ!" አሉ በድጋሜ ገጻቸውን እንደ መቋጠር አድርገው። ከዚያም ተማሪ ብሉይንና ሐዲሱን ተምሮ በጊዜ ወደ መጣበት ይመለሳል እንጂ እንዲህ ዐይነቱን ምሥጢር ጉርጉራ ምን አመጣው?።" አሉ ሊቁ ፋሬስ እንደ መበሳጨት ብለው።

ሊቁ ፋሬስ በጠቢቡ ተዋነይ ዙሪያ ሲጠየቁ እምብዛም ደስተኛ አይደሉም። በራሳቸው የደረሰው ምሥጢር በሌሎች እንዲደርስ ባለመፈለግ ዝምታን ይመርጣሉ።

"እሱስ እውነት ነው! ብሉይና ሐዲሱ መቅደም አለበት፣ ግንኮ የኔታ! ይህንንም መጠየቁ ክፋት የለውም። ቅኔ ቤት ሲኖሩ ሁሉም ነገር

ይጠየቃል:: ደግሞ ባለቅኔዎችን እስከ-ግብራቸው ስናውቃቸው ሥራቸውን እንደ ተምሳሌት ወስደን በታታሪነታቸው አርአያ እናደርጋቸዋለን::" አለ ሌላኛው ተማሪ ተደርቦ::

PDF Compressor Free Version

ፈርቶ ነው እንጂ ይሄ ጥያቄ እሱንም ናላውን ሲያዞረው ነው የኖረው:: "ብጠይቃቸውስ? ውጣ ከዚህ ቅኔ ቤት ብለው ቢያባርሩኝስ? ጎንጆች የተዋነይን ታሪክ ሌላ አሳስቶ ሲተርክባቸው ይቆጣሉ::" እያለ ሲጨነቅ ይኖር ነበር::

"ጥያቄው ስለ ቅኔአቸው አርአያነት ከሆነ ክፋት የለውም:: እንደ ሽጋ ቅኔ ይበል ያሰኛል::" አሉ ሊቁ ፋሬስ በመምህራን ልማድ ከብስጭት ወደ ትእግስት ተመልሰው::

ያ ሁሉ ተማሪ ጆሮውን እንደ ጥንቸል አቆመ::

"እንዲያውም ረስቼው ነበር...!" አሉ ሊቁ ሲጀምሩ::

"እንዲያውም ረስቸው ነበር:: መልካም አመጣችሁት! 'ተዋነይ! ተዋነይ!::" አሉ መሬቱን በአጭር ከዘራቸው እየቆረቆሩ::

ከዚያም "ተዋነይ የቅኔ ሰው ነው!::" አሉ በደፈናው::

"ስሙ ብቻ ከባድ ነው?" አለ ነበልባል ትንሽ ፈጠን ብሎ::

"አዎ! ተዋነይ ስሙም ቅኔውም ከባድ ነው:: ለጆሮም ሩቅ ነው:: አሁን ላለው አዲስ ትውልድ ደግሞ ስሙም ሆነ ፍልስፍናው ግራ የሚያጋባ ይመስለኛል:: ስሙ ለጆሮ ሩቅና አሰልቺ ስም እንደሆነ እኔም እረዳለሁ:: ምን ስሙ ብቻ? ፍልስፍናውም ዝኒ ከማሁ ያስብላል:: በደመና መሄድ ረቂቅ ፍልስፍና ነው:: ተዋነይ በሰለጠኑ ዓለማት ተወልዶ ቢሆን ከጥበቡ እስከ ቅኔው፣ ከስሙ እስከ-ፍልስፍናው ድረስ ብዙ ገድል የሚጻፍለት

PDF Compressor Free Version

ጠቢብ ነበር። በኢትዮጵያ ግን እስካሁን እሱን የሚገልጥ ታሪክ የተጻፈለት አይመስለኝም። የቅኔው ጠቢብ ተዋነይ 'ትኂን ነኝ' ሲል በራሱ አንደበት ተናግሮ ነበር። ስመ-ሙም 'ትኂን ነኝ' ካለው የጥበብ ሰው የተወረሰ ነው። ፍልስፍናው ግራ ያጋባል ያልኋችሁ 'ትኂን ነኝ' ሲል ራሱን የገለጠበት ጥበብ ገርሞኝ ነው። አላዋቂ ሰዎች ግን ተዋናይ ይሉታል። የቅኔው ሰው ትክክለኛው መጠሪያ ስም ግን ተዋንይ ነው። በእርግጥ "ተዋነይ! ስመ- ለጆሮ ሩቅ ስለሆነ ተዋናይ ቢሉት አይፈረድባቸውም። ቅኔ ቤት እስካልረገጡ ድረስ ስሙን ጠንቅቀው አያውቁትም። በዚያ ላይ ለሰነፍ አሰልቺ ስም ነው።" ብለው ቅኔ ቤጠ ተናገሩ።

ቀጥለውም:-

"ተዋነይ በደመና ይሂድ ነበር የሚለው ትንሽ እውነትነት አለው። ከዚህ ጎን ለጎን ባለቅኔው ተዋነይ ከቅዱስ ያሬድ በኋላ ተነሥቶ በቅኔ የተራቀቀ ሊቅ ሞምር ነው። በጥበብም ጸባያት ድረስ የተምዘገዘገ ፋና-ወጊ ጠቢብ ነበር።" አሉ ሊቁ ፋሬስ

"እንዴት? እንዴት?" አለ ከቀልቡ ያልሆነ አብሿም ተማሪ። አብሿሙ ተማሪ ጥንቱን የሊቁ የፋሬስ ደቀ-መዝሙር አይደለም። በየቅኔ ቤቱ እየተሳሳረ የሚኖር እግረ-ተማሪ ነው። በል ሲለው ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ሂድ ሲለው እንደ አሞራ ከሀገር ሀገር ይንከራተታል። እንዲህ ለእግረ-ተማሪነት የዳረገው ባለማወቅ የወሰደው አብሾ ሲሆን ቆላ ወርዶ፣ ደጋ ወጥቶ ይጀብራል። እግሩ ቅኔ ቤት ከመርገጥ በተር ቁጡ አይቀመጥም። ዛሬ አድሮ ነገ እንደ አብድ ውሻ ይፈተለካል። እሱ ግን "ጠላቶቹ በወፍ

ክንፍ ስለደገመብት እንደወፍ ብ..ር..ር..ብ..ር..ር.." እያለ ሀገራትን ማካለሉን እንጂ አብሮው ወፈፍ እንዳደረገው አያምንም:: በሰሞኑ ግን ትንሽ ረጋ ብሏል:: ከታብር ሲሳይ ለመቋደስ ጎንጅ ደብረ-ጥበብን ሙጥኝ ማለቱን እንደሊቅነት ቆጥሮታል::

"እንዴት? እንዴት?" ብሎ በግልምጫ ጭምር ሲጠይቅ ተማሪዎች ሊቁን በመዳፈሩ ገላመጡት::

ሊቁ ግን ያንን ተማሪ ከመጢፍ ሳይቆጥሩ ጥያቄውን መንቀፍ ጀመሩ::

"ዝም ብሎ 'በደመና ይጫን ነበር' ማለት የማይም ጥያቄ ነው:: ሊቅ መንሥኤውን ጭምር እንጂ መፍትሔውን ብቻ አይጠይቅም:: መጀመሪያ በደመና መሄድ ይቻላል ወይ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል::" አሉ ሥራቸው እንደ በገና ክር ግትርትር ብሎ::

"አዎ! ጥያቄው በሊቅነት ወግ መሆን አለበት:: በዚህ ሁሉ ሊቃውንት መኻል ብጡልና ቁንጽል ጥያቄ ማንሣት የየኔታን ጆሮ አይመጥንም::" አለ ሌላው ቀባጣሪ ተማሪ::

"እሱ ነው እንጂ ወጉ!" አሉ ሊቁ ደጋፊ በማግኘታቸው ደስ ብሏቸው:: ከዚያም "በሊቅነት ወግ ስትመጡ መልሱም በሊቅነት ደረጃ ይመለሳል:: በተለይ የተዋነይ ምሥጢር በቀላሉ የሚፈታ አይደለም:: ምን አልባት ውሉ ሲጠፋብን እንደ ተለመደው ተዋነይ ጠንቋይ ነው:: ተዋነይ አስማታም ነው:: ተዋነይ ከዛር የተደቀለ ነው ብለን ያለ ስሙ ስም ሰጥተን ጥያቄውን ካላለፍነው በቀር ምሥጢሩ ኃያል ነው::" አሉ ሊቁ ፋሬስ::

PDF Compressor Free Version

"ይኸንን ተራ ወሬማ ማንም አልፎ ሂያጅ ያወራዋል። ይህ ሁሉ በቅኔ ቤቱ እንደ አሸን የሚፈላ ተማሪ የሚፈልገው አማናዊውን ተዋነይ ነው።" አለ ነበልባል።

ትንኩሽቱ ነበልባል በቅኔ በኩል ሊቁ ፋሬስን ሊጥል ያንገዳግዳቸዋል። የመጣውም ቅኔ ብቻ ሊማር ሳይሆን ከተዋነይ ጥበብ ብቋደስ እንጂ ምሥጢር ይገለጥልኛል ብሎ ነው።

"አማናዊውን ተዋነይን ነው ማወቅ የፈለጋችሁት?" አሉ ሊቁ ፋሬስ ተማሪዎችን በአንክሮ እየተመለከቱ።

"አዎ! እሱን ማውቅ ነው የምንፈልገው?" አለ ነበልባል።

ተማሪዎች በነበልባል ሐሳብ በአንድ ትንፋሽ ተስማሙ።

ሊቁ ቀጠሉ።

"አማናዊው ተዋነይ የተወለደው ከዚህ አኅጉጅ ደብረ-ጥበብ ገዳም አፍ ብሎ ከአፋፉ ሳይ ነው ይላሉ ታሪክ አዋቂዎች። የቅኔው ሊቅ ዕቡይ ካሣና ማዕበል ደሴም የተፈጠሩት ከዚያው ግድም ነው። የኅጉጅ ቅኔ መንገድም ምንጩ ከዚሁ ኅጉጅ ደብረ-ጥበብ ነው። ከቅኔውና ከጥበቡ በቀር ስለ ተዋነይ መዋዕለ-ልደት ግልጥ ያለ የሰነድ ማስረጃ የለም። በቅኔ በኩል ግን እስከ አሁን ከጫፉ የሚደርስ የቅኔ ሊቅ አልተፈጠረም። ከመምህር ሳይማር ቅኔ ስለተገለጠለት ከመምህር ከተማሩ ሊቃውንት ይለያል። እንደቅኔ መምህርነቱ የተዋነይን ገድል ብዙ መርምሬያለሁ። ገድሉም አስደምሞኛል። እናንተ ግን በቀላሉ ትረዱታላችሁ ብዬ አላምንም። እንዳሰረዳችሁም አትንዝንዙኝ። ስለተዋነይ መጨቃጨቅ ሰልችቶኛል። ጠቢብነቱን ለማስረዳትረጅም ርቀት ሄጀ ነበር። ነገር ግን

PDF Compressor Free Version

እስካ[illegible] ስዚብ አላገኘሁም:: እናንተም ብነግራችሁም ገድሉን ማመን ያቅታችኋል:: ለአእምሯችሁ ከባድ ነው::" ሊቁ ፋሬስ ተሰላቹ::

"ለአእምሯችን ሊከብድ ይችላል:: ማመኑን ግን በደንብ እናምናለን::" አለ ያ ቀጫጫ ተማሪ ጥያቄውን በማንሣቱ ኩራት ተሰምቶት::

"ጥሩ!:: እንዲያው አእምሮችሁ ይህን ያኽል ከበሰለ ወደፊት በተዋነይ ዙሪያ መወድስ ቅኔ እዘርፋለሁ:: ከቅኔው ሐሳብ እየተነሣን ስለ ተዋነይ ጥቡብም ሆነ ስለሌሎች ሀገራዊ ምሥጢር በግልፅ እንነጋገራለን::" አሉ ሊቁ ፋሬስ::

ያ ሁላ ተማሪ በደስታ ፈነጠዘ:: የዕለቱ ጉባኤ በዚህ አልቆ ሊቁ ወደ ቅኔ ዘረፋ አመሩ::

PDF Compressor Free Version

ሐምሌ ጨላልሚል። በጨለማ ላይ ክረምት፣ በክረምቱ ላይ ዝናም፣ በዝናሙ ላይ ጉም ተጨምሮበት ወርኑ-ክረምቱ ጨፍግጓል። ጎንጅ ደብረ-ጥበብም ጭቃ በጭቃ ሆናለች። የዋልካው ጭቃ ከአግር ጋር ሲጣበቅ አብሮ የተፈጠረ ድርብ ሥጋ፣ ትርፍ ገላ ይመስላል። የጎንጅ ሰዎች ጥልፍልፍ ጫማቸውን ከጭቃው ጋር መሸከም ስላልቻሉ በባዶ እግር መሄድን መርጠዋል። በዋሽራ በኩል ያለው ጥቁሩ ሰማይ ከገመገሙ ተራራ ጋር በመርፌ የተሰፋ ይመስላል። እንደ አሮጌ ጨርቅ ጨርደድ የሚለው የመብረቅ ድምፅ የዓለምን ፍጻሜ አቅርቦታል። ከጎንጅ ደብረ- ጥበብ በደቡብ በኩል ያለችዋ የቅኔዋ ሀገር ዋሽራ ማርያም በጉምና በቅኔ ተጀቡናለች። በጋ ተክረምት ወደ ቆላው ጥሬ ልመና የሚወርዱት የዋሽራ ማርያም የቅኔ ዘራፊዎች በሰሞኑ ወደ ቆላው ብቅ ብለው አያውቁም። ጉልቻ ጉልቻ የሚያካክል ድንች ለመለመን ወደደጋው የሚገሰግሱት የጎንጅ ደብረ-ጥበብ የቅኔ ተማሪዎችም ወደደጋ መውጣት አቁመዋል። ሁለቱን ቅኔ-ቤቶች መወድስ አንድ ቢያደርጋቸውም ተፈጥሮ አራርቋቸዋል። የክረምቱ ክብደት ከፋፍሏቸዋል። በዋሽራ ማርያም በኩል የጉም ጭራ ውኃ ውኃ ይላል። በጎንጅ በኩል ደግሞ አሸኖች ይርመሰመሳሉ። የጎንጅ ሰዎች ነጭ ጤፍ ይዘራሉ። የቅኔ ተማሪዎች ጥበብ ያመርታሉ። በጎንጅ ደብረ-ጥበብ ሌሊቱ ይነጋል። ጀምበር ትፈልማለች። ምድር ይመሻል።

PDF Compressor Free Version

፯

ቅኔ ዘረፋ ጊዜ

ሐምሌ ጨላልሟል። በጨለማ ላይ ክረምት፣ በክረምቱ ላይ ዝናም፣ በዝናሙ ላይ ጉም ተጨምሮበት ወርኃ-ክረምቱ ጨፍግጓል። ጎንጅ ደብረ-ጥበብም ጭቃ በጭቃ ሆናለች። የዋልካው ጭቃ ከእግር ጋር ሲጣበቅ አብሮ የተፈጠረ ድርብ ሥጋ፣ ትርፍ ገላ ይመስላል። የጎንጅ ሰዎች ጥልፍልፍ ጫማቸውን ከጭቃው ጋር መሸከም ስላልቻሉ በባዶ እግር መሄድን መርጠዋል። በዋሽራ በኩል ያለው ጥቁሩ ሰማይ ከገመገሙ ተራራ ጋር በመርፌ የተሰፋ ይመስላል። እንደ አሮጌ ጨርቅ ጨርደድ የሚሰው የመብረቅ ድምፅ የዓለምን ፍጻሜ አቅርቦታል። ከጎንጅ ደብረ- ጥበብ በደቡብ በኩል ያለችዋ የቅኔዋ ሀገር ዋሽራ ማርያም በጉምና በቅኔ ተጀቡናለች። በጋ ተክረምት ወደ ቆላው ጥሬ ልመና የሚወርዱት የዋሽራ ማርያም የቅኔ ዘራፊዎች በሰሞኑ ወደ ቆላው ብቅ ብለው አያውቁም። ጉልቻ ጉልቻ የሚያካክል ድንች ለመለመን ወደደጋው የሚገሰግሱት የጎንጅ ደብረ-ጥበብ የቅኔ ተማሪዎችም ወደደጋ መውጣት አቁመዋል። ሁለቱን ቅኔ-ቤቶች መወድስ አንድ ቢያደርጋቸውም ተፈጥሮ አራርቋቸዋል። የክረምቱ ክብደት ከፋፍሏቸዋል። በዋሽራ ማርያም በኩል የጉም ጭራ ውን ውን ይላል። በጎንጅ በኩል ደግሞ አሸኖች ይርመሰመሳሉ። የጎንጅ ሰዎች ነጭ ጤፍ ይዘራሉ። የቅኔ ተማሪዎች ጥበብ ያመርታሉ። በጎንጅ ደብረ-ጥበብ ሌሊቱ ይነጋል። ጀምበር ትጨልማለች። ምድር ይመሻል።

ሊቁ ፋሬስ ያለ ወትሯቸው ገጻቸው ሾላ እንደመሰለ ከቅኔ ወንበራቸው ላይ ተPDF Compressor Free Versionቀ እንደተለመደው ሁለት ሦስት ግስ አስምተው ‹‹ተቀበል!" አሉ ቅኔ ሊዘርፉ እየተዘጋጁ:: ተረኛው ቅኔ-ተቀባይ ተማሪ ጉሮሮውን አጽድቶ ተከተላቸው::

"ተዋነይ ሀበኒ ከመ አርከለዲስ ወዓሊ፤

ሊሳየ-ጠቢባን ጥበበ እንተ አትረፈቶ ጠሊ::" አሉ ሊቁ ፋሬስ በምሽቱ የቅኔ ዘረፋ ጊዜ ተዋነይ ትዝ ብሏቸው:: በዚያውም የተዋነይ ፍልስፍናን ቀስ በቀስ በተማሪዎች ልቡና ለማሥረጽ ፈልገው::

ከዚያም ወደ ትርጉሙ ተመልሰው

"ተዋነይ ጠቢቡ አንተ የጥበብ ሰው፤

ከአርከለዲስ ጥበብ ከተትረፈረው፤

አንድ ጉራሽ አቅምሰኝ ፍየል ካተረፈው::" አሉ::

ቅኔ ተቀባዩ ተቀበላቸው:: ቅኔውን ዘርፈው እንደጨረሱ ተማሪዎች የገባቸውንም ያልገባቸውንም ቀለም ሲጠይቁ ሊቁም የተማሪዎቹን ጥያቄ ሲቀበሉ ቆይተው ጨርሰው ከወንበራቸው እንደተነሡ፤

"የኔታዬ" አለ ነበልባል::

"አቤት" አሉ ሊቁ::

"አርከለዲስ ማን ነው? ታሪኩን ቢነግሩን?" አለ ነበልባል የአርከለዲስ ስም ለጆሮው እንግዳ ሆኖበት::

ሊቁ የነበልባል ጥያቄ እንደ ዋዛ የማይታለፍ እንደሆነ ሲገባቸው አፋቸውን በመሐረብ እያሻሹ ተመልሰው ወደ መንበራቸው ተሰየሙ:: እንደ ገና እንደ አዲስ ጉባኤ ጀመሩ:: የአንጋፋ ሊቃውንት ወግ ነው::

PDF Compressor Free Version

አንጋፋ ሊቃውንት ቀለም እየተጠየቁ ዝም ብሎ የመሄድ ልምድ የላቸውም። ነውር ነው። ሊቁ ፋሬስም የአንጋፋዎች አንጋፋ ስለ ሆኑ ሲጠየቁ በአርጋታ ይመልሳሉ። ቀለሙ እንዳይነጥብ ይጠነቀቃሉ። ታሪክ እንዳይፋለስ ይጥራሉ። የሚያውቁትን አጥርተው ያስረዳሉ። ከወቅማቸው በላይ የሆነውን ጊዜ ይግለጸው ብለው በጸሎት ወደ ፈጣሪያቸው ይጮኻሉ። ወይም ንባብ ላይ ያዘወትራሉ። ቀለም ገፍቶ መሄድ ግን በጭራሽ ነውር ነው። ስለዚህ ጉባኤን ጨርሰው እንደ ገና አዲስ ጉባኤ ጀመሩ። ከመንበራቸው ላይ እንደ ቆመ የመውደቅ ያኽል ዘ..ፍ..ፍ አሉ።

ከመንበራቸው ላይ ተደላድለው ከተቀመጡ በኋላ "አርከለዲስማ! ከተዋነይ ደቀ መዛሙርት አንዱ እንደ ነበር ታሪክ ይናገራል።" አሉ።

"እሽ" አለ አንድ ተማሪ።

ያ ሁሉ ተማሪ ገጹ ፈካ።

"አርከለዲስ በተዋነይ ቅኔ ቤት ብዙ ዓመታትን አሳልፏል። ቅኔ ሲማር መጦቱ የፍየል እረኛ እንደሆነ ወግ አዋቂ፣ ታሪክ ነጋሪ ሰምች ይናገራሉ።" አሉ ሊቁ ፋሬስ ድንቁ።

ያ ሁሉ ተማሪ ተቁለጨለጨ።

ሊቁ በትዝታ ፈረስ ወደ ኋላ ሸመጠጡ። ተማሪዎች ይበልጥ በኩራዟ ብርሃን እያጮለቁ ዐይኖቻቸውን አነጣጠሩባቸው። እኔ ባልደርስም ሲወርድ ሲወራረድ የመጣው የአርከለዲስ ምሥጢር ደርሶኛል። ተማሪ በነበረበት ወቅት የተዋነይ ቅኔ ቤት ተቃጥሎ ነበር ይባላል።" አሉ

PDF Compressor Free Version

በድጋሜ በረጎብ የደበዘዘ ገጸቸውን በእጃቸው ከናፍሮቻቸውን በመሐረብ እያሻሹ። በተማሪዎች አንደበት ዝምታ ሰፈነ።

ቅኔ ቤቱ ሲቃጠል ሊቃውንቱ አሳቱን ለማጥፋት መራወጥ ጀመሩ። ገሚሶች በዛፍ ግንጣይ ለማጥፋት ሲረባረቡ ከፊሎቹ ደግሞ ውኃ እየቀዱ በአሳቱ ላይ ቸለሱበት። አሳቱ ግን ቤንዚን እንደተርከፈከፈበት እየጋመ ሂዶ የተማሪዎችን ጎጆ ዶግ ዐመድ አደረገው። ተማሪው አንደዐቅሙ መጽሐፍ ያለው መጽሐፉን፣ ደበሎ ያለው ደበሎውን፣ ዳባ ያለው ዳባውን፣ ለምድ ያለው ለምዱን፣ ድራቶ ያለው ድራቶውን፣ ከአሳተ-ገሞራ አወጣ። ንዝ መሸከፍ ያልቻለው ደግሞ እግሬ አውጭኝ ብሎ ከአሳቱ ለመራቅ ተራወጠ። ቀውሴ የሚባል ልክስክስ-ቢጤ ተማሪ ነበር አሉ። ቀውሴ የቅጽል ስሙ ሲሆን ቅጽሉን ከንደኛቹ ነው ያገኘው። ትንሽ ቅራሪ ሲቀምስ ተደባዳቢ ስለነበረ ቀውሴ ተባለ። እናም ቀውሴ እቃ ሊያወጣ ወደ ጎጆው ሲገባ የተካቻረ ኮቾሮ አግኝቶ ሲበላ ነፋስ የአሳቱን አቅጣጫ ቢያስቀይረው የአሳቱ ላንቃ ሳይታሰብ ወደእሱ ዞረና የጎረሰውን ሳይውጠው እዚያው ዐመድ ሊያደርገው ሲል እንደምንም ተስፈንጥሮ ያችን የተማሪ ጎጆ ባንድ እርምጃ ተራመዳት። የቅኔ ቤቱ ጎጆዎች ዐመድ ሆነው ሲያልቁ የአርከለዲስ ጎጆ እንደጸድቅ ሽንብራ ከመካከል ፈጥጣ ቀረች። ተማሪዎች ያችን ተአምረኛ ጎጆ እንቧለሉ እየዞሩ አርከለዲስን ማፈላለግ ጀመሩ። ያንን ያኽል አሳተ-ገሞራ ፉንድቶ ሀገር ሊያልቅ መጽሐፍ ዘርግቶ በአሳቱ ወጋገን በላንቃዉ ብርሃን ሲያነብ ተገኘ።

ከዚያ በፊት ቅኔ-ቤት ከመቼ ጀምሮ እንደመጣ ሊመረመር ቅኔ ከጀመረ ሦስት ዓመት ሆኖት ነበር። እስከዚያች ቀውጢ ቀን ግን

PDF Compressor Free Version

በመልክ የሚያውቀው ፍጡር አልነበረም። ቅኔም አልገባው ሲሉ 'ደጓዕሌ' የሚል ቅጽል ተሰጥቶት ራሱን ከሊቃውንት ሰፈር አግልሎ ይኖር ነበር" አሉ ሲቄ ፋሬስ ድንቁ አሮር ከዘራቸውን እያወዛወዙ። ያ ሁሉ ወሬ ሰማይ ተማሪ ቀሪውን ጉድ ለመስማት ጆሮውን አቆመ። ሲቄ ቀጠሉ፤

"መልኩም" ቀይ ፋም የመሰለ መልከ መልካም ሞዛዛ ቢጤ ነበር። ወደ ተዋነይ ቅኔ ቤት የመላው ቅኔ ሊማር ነበር ይባላል። ከቅኔ ቀድሞ አከከ ወረረው ጉጃፋር የሚባል ደዌ በሰውነቱ ቡግር ቡግር አለሰ። "አከ ዘተምሕረ፥ ይከውን መምሕረ" ያለው የአበው ብሒል ሳይገዛው በጉጃፋሩ ፈጣኖ ተማረረ። በቅኔው እምብዛም ሳይገፋ ቅኔውን እርግፍ አድርጎ ትቶ የፍየል እረኛ ሆነ።"

"ያን ጊዜ ተዋነይ የሚተዳደረው በፍየል እርባታ ነበር ማለት ነው?" አለ ነበልባል።

"አይደለም! አይደለም!" አሉ ሲቄ።

"ታዲያስ?" አለ ጥያቄውን ያመጣው ነበልባል።

"ተዋነይ በፍየል እርባታ የሚተዳደር ሰው አልነበረም። ቀድሞውንም ፍየሎች ሰርቢ ታስበው የተሰበሰቡ አልነበሩም። ለአንዳንድ ምሥጢራዊ ጉዳይ ከዚያም ከዚያም የተለቃቀሙ እንጂ" አሉ ሲቄ ፋሬስ።

"ለምን ነበር የተሰበሰቡት?" አለ አሁንም ነገረኛው ነበልባል።

"በመምህር አምላክ የደመርሁትን ልጨርስ?" አሉ ሲቄ ስለ አርከለዲስ ሳይጨርሱ ታሪኩን ታሪክ፣ ወጉን ወግ፣ አየሳበው ሲሄድ አይተው።

"እሺ የኔታዬ" አለ ሌላው ቀጫጫ ተማሪ በትሕትና።

PDF Compressor Free Version

"እንዳልኋችሁ አርከለዲስ ከትምህርት ትሕትና ይቅደም ብሎ ፍየል ማንጋጋቱን ቅኔ ከመቁጠር፣ መወድስ ከመዝረፍ ቆጠረው። ጥቂት ቆይቶ ሰውነቱ መነመነ። ፍየል ሲከተል እየዋለ ምላሱ እንደፍየል ሲፈጥን እግሩ ከፍየል እግር ቀጠነ። ፊቱ ሞጨሞጨ። አጥንቱ ወጣ። ጉባኤው 'ምነው የመጣበትን ተምሮ ሳይመሽ አገሩ በገባ? ገና ለገና ተዋነይ እንደ ፍየሏ በቀዝቃዛ ውኃ ቅኔ ያዘርፈኛል። ከኋላ ተነሥቼ እቀድማለሁ።' ብሎ የፍየል መንጋ እያንጋጋ ፍየል እያዋለደ ቅኔውን ረሳው ብሎ መሳቂያ አደረገው።" ብለው ትንሽ ትክዝ አሉ።

በትረካቸው ገፉበት።

"ከጊዜ በኋላ ይህንን ስሰማ እኔም በሳቅ ነበር የፈረስኩት። አለማወቅ ነገር? ይህ ጥርሴ ያን ጊዜ አብሮ ስቋል! የከንቱ ከንቱ ነኝ! ፍየል እየጠበቀ ያገኘውን ነገር መመራመር ሲገባ መግቅን ምን አመጣው? እሱ የፈለገው ሌላ ነበር።" ብለው ያን ጊዜ ሳይገባቸው በሳቁት ሳቅ በሠሩት ሽሙጥ ውስጣቸውን ወቀሱ።

ሊቁ ፋሬስ እንዲህ ናቸው። አልፎ አልፎ ያለፈ አላዋቂነታቸውን ይወቅሳሉ። ደስ የሚል ምሥጢራዊ ቅኔ በተቀኙ ቀን ለብቻቸው ይሆኑና "አይ ፋሬስ! ሊቅ እኮ ነህ! መወድሱን እንዴት አድርገህ አሳመርኸው! ይላሉ በጣታቸው ወደራሳቸው እያመለከቱ። ቅኔው ደስ የማይላቸው ከሆነም ለብቻቸው ሁነው "አይ ፋሬስ! ዛሬስ አበላሸኸው! አሁን ይሄን ቅኔ ብለህ ትቀኘው? ፋሬስነትህ ጠፋ ማለት ነው? ብቻኸን ስትቀር ምን ታደርግ?።" ይላሉ።

PDF Compressor Free Version

ሊቱ የቀን ተቀን ሥራቸው ቅኔ ከመዝረፍ ጎን ለጎን በተዋነይ ጥንታዊ ፍልስፍና ላይ ምርምር ቢጤ መሥራት ነው። ከምርምራቸው ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ተዋነይ በታብር ምን ይሠራ ነበር? የሚል ነው። ጥናታቸውን በመጽሐፍ መልክ ጠርዘው ለተማሪዎቻቸው ማስረከብ ፈልገዋል። አስቀድሞ ግን በሊቃውንቱ ልቡና እንዲሳል ቀን በቀን እንዳንድ ቅኔ በተዋነይ ሰብአናና በቅኔው ፍልስፍና ቅኔ ይዘርፉሉ። በቂ ጥናት ያጠናሉ። ባንድ ወቅት የሞከሩት ጥናት ግን ዛሬ ድረስ ፈግግ ያደርጋቸዋል።

"ከአርከሰዲስ ወደ ፍየሎች ስመጣ..." አሉ ሊቁ ፋራስ ሻሻቸውን እያስተካከሉ።

"...ከአርከሰዲስ ወደ ተዋነይ የፍየል መንጋ ስመጣ ተዋነይ በእንዳንድ ነገሮች ላይ ሊጠበብ ከተፈጥሮ ተነሥቶ ነው። ለምሳሌ በደመና የመሄድን ፍልስፍና የጀመረው በአሰማት ሳይሆን ተፈጥሮ በሰጠችው ደመና ላይ ጥበብ ጨምሮ ነው። አዘመናት በፊት ደግሞ ሊቁ ተዋነይ የእኔ ፍየል ከበለዓም አሽያ አታንስም። እንዲያውም ትበልጣለች። እንደ መርቆሬዎስ ፈረስ ተአምር መሥራት ትችላለች። እንደ በለዓም አሽያ በልሣነ-ብዙኃ ታወራለች። እኔ ስሞት ፍየሌ የቅኔ መምህር ሆና መቀጠል አለባት። ቅኔ ቤቱ መዚጋት፣ ጉባኤው መታጠፍ የለበትም። ይህንን ተአምር ዓለም እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ። እኔም ከበለዓም እበልጣለሁ። ፍየሌም ከአሽያዋ ትልቃለች የሚል ፍልስፍና አደረበት። ይህን ፍልስፍና ለሊቃውንቱ ለመግለጥ ከመንጋው አንዲት ፍየል መርጦ 'ዘታብር' አቋደሳት። ያ ተባታሪ ምላሷ ከታብር ውኃ ጋር

PDF Compressor Free Version

ተደምሮ ያስቀባጥራት ጀመር። ቅኔ መዝረፍ ጀመረች። መወድስ አፈሰቀች። እንደባለቅኔ ተቁነጠነጠች። ፍየሏ መወድስ ስትዘራ ለአእምሮው ቢረዳውም ለተዋነይ ልሣነ-ሰብአንና ልሣነ-ጠሊን ለማዛመድ የሚያስችል ጥበብ አልነበረውም። ሊነጥቃት ፊልጳ አቃተው። እንደተመኘውም የቅኔ መምህር ሆነ ቅኔ ቤቱን ማስቀጠል እንደማትችል ተረዳ። በዚህ ባዶነት ተሰማው። ጥቂት ቆይቶ ሌላ መላ መጣለት። አባ መላ ተዋነይ ፍየሏን አርዶ አመራርዶ በመረቁ በኩልየ ታብርን ምሥጢር ያለ ምንም ድክም ወደ ሰው ልጅ አእምሮ ማስተላለፍ ፈለገ። የፍየሊቱን መረቅ እንደ ዓሣ ዘይት ለሊቃውንቱ ግቶ ብሩህ አእምሮ መፍጠር አማረው። ወዲያውኑ ፍየሏን አርዶ አመራርዶ ለሊቃውንቱ አብልቶ የታብርን ክሣቱ-ምሥጢርነት በመረቅ ለውሰ፣ በጠላ ጠንሰሶ ለትውልድ ማስተላለፍ አሰበ። ፍየሏ መወድስ እየዘራች ቅኔ እየዘረፈች በስለት ታረደች። ሥጋዋን እጎቱ ዐደይ ወጥ እንድትሠራው ተዋነይ አዘዘ። ደቀ መዝሙሩ አርከለዲስን ጨጓራዋን አጥቦ እንዲመጣ ወደ ወንዝ ላከው። ዐደይ ከወጡ ስትቀምስ ቅኔ ዘረፈች። ሌላም ለሌት አእምሮ የከበደ ምሥጢር ጸነሰች። ደቀ-መዝሙሩ አርከለዲስም በዘኩሉ ከፍየሏ ጨጓራ በሸንበቆ ሰንጠ ቆርጦ ቢቀምስ አእምሮው በእውቀት ተመላ። መወድሱ ከውስጡ ፈላ። ወዲህም ተዋነይ በደመና ተጭኖ የሚሄድበት ምሥጢር ተገልጦለት ከወንዙ እስከ ቅኔ ቤቱ እንደ ተዋነይ በደመና ተጭኖ ተመለሰ። ቀሪውን ምሥጢር ከተዋነይ ጋር በመመካከር ደበቁት። ውኃዋንም ተዋነይ በጥበቡ ሰወራት።

በቅኔዬ፡-

PDF Compressor Free Version

"ተዋነይ ጠቢቡ አንተ የጥበብ ሰው፣

ከአርከለዲስ ጥበብ ከተትረፈረው፣

አንድ ጉራሽ አቅምሰኝ ፍየል ካተረፈው:: ያልሁት እሱን ነው::" አለ ሊቁ::

"ስ..ስ..ወ..ራ..ት..?" አለ ነበልባል እንደ መቃዠት እየቃጣው::

ሊቁ ከወንበራቸው ላይ ብድግ ብለው በአቡሻክር ቀመር ሰዓት መስፈር ጀመሩ:: የአቡሻክሩ ቀመር ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት እንደሆነ ነገራቸው:: የጸሎታቸው ሰዓት ስለ ደረሰ የነበልባልን ጥያቄ ሳይመልሱ ወደ ቤታቸው ገሰገሱ::

PDF Compressor Free Version

፰

ዐበቅ የለሽ-ኅንደር

ጠቢቡ ሐረ ወደ ዐበቅ የለሽ ገሰገሰ። ዐበቅ-የለሽ ሰፈር አምሮባታል። አዝማሪዎቿ አዳዲስ ግጥም እየገጠሙ መሸተኛውን ያዝናናሉ። ጥበቃው ማንደፍሮ ከአዝማሪዎች በሚወረወርሰት የመገሳ ቅኔ ፈገግ ይላል። አልፎ አልፎ ደግሞ ለራሱ ታላቅነት ይሰማውና አመልካች ጣቱን ከላዕላዊ ከንፍሩ ላይ አሳርፎ እንደ ባለቅኔ ትንሽ ይመሰጣል። ከዚያም ክራሻቱን እያስተካከለ ዘና ይላል። ክራሻቱ ከጀርመናዊ ባለ-ሀብት በስጦታ ያገኘው ነው። ክራሻቱ ጥቁር አንገት የተቀጠለለት ፈረንጅ አስመስሎታል። መሸተኛው ከጠጅም ከአረቂውም ቀማምሰ ሞቅ ሲለው ወንበሩን እየሳበ ወደ ማንደፍሮ ተጠጋ። ማንደፍሮ የእጨጌ ቤትን ጉዳይ ያወራቸው ዘንድ የጎንደር የቁርጥ ቀን ልጆች ይወተውቱ ጀመር። ማንደፍሮ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጀርመናዊዉ እንደ ክላውንስ፣ ሌላ ጊዜ እንደ ማንደፍሮነቱ መመለስ ጀመረ።

ጠቢቡ ሐረ የትናንት ማንነታቸውን ከማንደፍሮ ሰመደበቅ በላዩ ላይ ሰሦስት መበለቶች ለቆብ የሚበቃ ረጅም ሻሽ ደግለለው በሻሹ ዙርፍ ብሩህ ፊታቸውን ደብቀው ጥበቃው ማንደፊሮ ድሮ ስመኒ፣ ዘንድሮ ዩሮ፣ እየመነዘረ ጠጅ ከሚጠጣበት መሸታ ቤት ተገኙ። እንዳይጠረጥር ራቅ ብለው ጠጅ በጠርሙስ አስቀርበው የሚጠጡ መስለው ማንደፍሮ የሚያወራውን ማዳመጡን ተያያዙት። ጠጅ የሚጠጡ ለመመስል ጠርሙሱን ከከንፈራቸው አድርሰው ይመልሱታል።

በመ'ኻል

PDF Compressor Free Version

"ማንዴ የቤቱ ጉዳይ ከምን ደረሰ?" አለ አንድ ሞቅ ያለው ጅግና ንንደራ።

"እስካሁን ከመዳፌ አልወጣም። ጠብ-መንጃዬን ወድሬ እየጠበቅሁ ነው። ብዙ ጠንራ-ልውጥ ሰዎች በጠፋ በረር እየቃኙት ቢሆንም ወደ ውስጥ እንዲዘልቁ ግን አፈ-ሙዜ አትፈቅድም። ክንፍ አልባ መልአክ ነው የማደርጋቸው።" አለ ማንደፍሮ።

"የሊቃውንቱ ጉርምርምታስ ምን ላይ ደረሰ?" አለ ያው ሰውዬ መልሱ።

"ይህ ጠምጣሚ ሁላ! ምን ያመጣ ብለህ ነው! እኔ ማንደፍሮ!" አለ በወኔ።

"መንግሥትስ ለቁሶች ምን መፍትሔ እያመጣ ነው ቤቱን ሊመልስ ነው ወይስ?..."

"ጉዳዩ ገና አልተቋጨም። ሊቃውንቱ ከመንግሥት ጋር መንግሥትም ከቁሶች ጋር ግብ ግብ እንደ ገጠሙ ናቸው። ቁሶች መንግሥት ላይ ያመፁ ይመስላሉ። መንግሥትም እንደ ድሮው ነገሩን በኃይል መፍታት የፈለገ አያመስልም። ካህናቱን እየተሰማመጠ ይገኛል።" አለ ማንደፍሮ ጠጅን እየተጎነጨ።

"ምነው ልምምጡ?" አለ ሞቅ ያለው አንድ ሌላ ቀጭን ጅግና።

ማንደፍሮ የብርሌዋን አንገት ጨብጦ ጠጁን ኩተጎነጨ በኋላ፣

"ልምምጡስ ግራ ያጋባል። መንግሥት ካህናቱ በሃይማኖት ሰበብ ሕዝቡን ይቀስቅሰብኛል ብሎ ነገሩን በምሥጢር ይዞታል። ካህናቱም "የእጨጌው ቤት ከሊቃውንቱ የሚወጣ ከሆነ እንደ ፋሲካ በማ እንታረዳለን። ሰማዕትነት ሊያመልጠን አይገባም" እያሉ በመስቀል

PDF Compressor Free Version

እየማሉ ናቸው። ቀሃ ወርደው የተማማሉም አልጠራም።" አለ ማንደፍሮ።

"እረ ለመሆኑ ይህንን ቅርስና ቅዱስ ቤት ደፍሮ የገዛው ማን ነው?" አሉ አንድ በእድሜ ጠና ያሉ የደስ ደስ ያላቸው አረጋዊ። ሊቅ ዐፅቁ ነበሩ።

"ገዢው ባሕር ማዶ ያለ ጀርመናዊ ነው። ባለፈው ሳምንት ቤቱን ሊረክብ መጥቶ አይቸዋለሁ። በመኻል ግርግር ሲነሣ የመንግሥት አካላት እንደ ንጠር መ·ሸራ ሸፋፍነው ወሰዱት።" አለ ማንደፍሮ።

"ግርግር? በስመ አብ ወወልድ! ወመንፈስ ቅዱስ! ከዚያም ተደርሷል?" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ።

"አሥ እንጂ ጠቡ ያለ ደም የሚበርድ አይደለም። እኔም አንድ ቁስ በእጁ ሳይጠፋ የሚቀር አይመስለኝም።" አለ ማንደፍሮ።

"ተዉ እንጂ አያ ማንደፍሮ? ባሕር ተሻግሮ የመጣ ዜጋ ደስ ይበለው ብለህ እንዴት የካህን ደም ታፈላለህ? ካህን ቢገድሉት መቼ ይሞትና! ደሙ ጠብ ሲል ደሙን መሬት አይጣጣውም። ደሙ እየፈላ ሲከስህ ይኖራል። በዘያውስ ላይ እኛ ጎንደሮች ካህን ከነፍሳችን በላይ እንደምንወድ ታውቅ የለ?። እንዳትነካካ።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ።

"እኔ ካህን የምገድለው ለጀርመናዉዊ ብዬ አይደለም።" ብሎ የብርሌዋን አንገት ጨበጠ..."

በረጅሙ ተንፍሰው፡-

"የድሮ ማንደፍሮ ሚዞ ሳንቲም ያልነበረኝ መናጢ ደኃ ነበርሁ። ጠጅ ሲሸተኝ ውሎ ሲሸተኝ የሚያድር ምስኪን ደሃ ነበርሁ። አሁን ግንዘሥራዬ የማገኘው ዩሮ ጨመርመር እያለ ነው። የሀገሬ መንግሥት

PDF Compressor Free Version

በወር አምስት መቶ ብር ሲከፍለኝ ጀርመናዊ ደግሞ ከጉርሻው ሌላ ወርኃዊ ደመወዝ ሦስት መቶ ዩሮ ይከፍለኛል። እንዲያውም ይህ ለጊዜው ነው። ቤቱን ሲረከብ በእጥፍ እንደሚጨምርልኝ ቃል ገብቶልኛል። በክብሬና በደመወዜ የቀኑ ካህናት ግን በሥራዬ እየገቡ ናቸው።" አለ ማንደፍሮ።

"አይደለም። ሦስት መቶ ዩሮ ቀርቶ እልፍ አእላፋት ዩሮ ይከፈልህ። በእጅህ ግን የሰው ነፍስ እንዳይጠፋ። ደም እንዳይፈስስ።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ።

"ፈጣሪ ሞት ያዘዘበትን አላውቅም እንጂ ደም መፍሰሱ አይቀሬ ይመስለኛል። በተደጋጋሚ በሕልሜ አፈ-ሙዜን ደም ስቀባ ነው የማድረው። መልአኩ-ሞት የጠራው የሕልሜ ሲሳይ መሆኑ አይቀርም። እንዲያውም ከትናንት በፊት አንድ ልጅ እግር መለኩሴ ቢጤ መጥተው የሕልሜ ፍቺ ሊሆኑ ነበር። ከሰይጣን ጋር ታግዬ እኔ አሸነፍሁ። መነኩሴው ተረፉ። ወደ ፊት ሰይጣን ካሳሳተኝ እሳሳታለሁ። ይልቅስ ቁስ የገደለ ንስሓው ስንት ዓመት እንደሆነ ካወቁ ይንገሩኝ?። ከጦሙም ከቀኖናውም እንዲያግዙኝ።" ብሎ ወደ ጠጁ አቀረቀረ። ጠጁን ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ ቀና ብሎ ዙሪያ ገባውን ሲቃኝ ከጠቢቡ ሖረ ጋር ዐይን ለዐይን ተጋጨ። ማንደፍሮ ሖረን ሊውጣቸው ደረሰ።

"አላልኋችሁም!፡ እየተከታተሉኝ ነው! እገድላቸዋለሁ! በሥራዬ ከገቡቡኝ ካህናት መኻል እኒህ ጠጉረ-ልውጥ ቀዳሚው ናቸው። ትናንትና መለኩሴ መስለው መጥተው ሊገድሉኝ ሲሉ በጥረቴ ዳንሁ። ዛሬ ደግሞ

PDF Compressor Free Version

ከጠጁ ጋር ሥራይ ሊያደርጉብኝ፣ መተት ሊመትቱብን መምጣታቸው ነው። እፋለማቸዋለሁ!።" ብሎ ግብ ግብ ገጠማቸው።

ማንደፈሮ የፈረጠመ ክንዱን ሊያሳርፍባቸው ሕቅ ሲሉ ነበር። በመኻል ሊቅ ዐፅቁና ያው ጀግና በሆኑ በግልግል ብዛት ተረፉ። ማንደፍሮ ለያዥ ለገራዥ ቢያስቸግርም መጨረሻው በሊቅ ዐፅቁ ጥሪት ጠቡ ጥቂት በረደ አለ። ማንደፍሮ የጠጁን ብርሌ አንሥቶ ብዙ ከተገለገለ በኋላ ብርሌዋን እንደ ጨበጠ እየፎከረ ወደ እጨጌ ሰፈር ክላሹን ሊያመጣ በረረ። ሊቅ ዐፅቁ ዐይኔ እያዬ ሰው ሲሞት ዝም አልልም ብለው ጠበቡ ሖረን ይዘው ወደ ቤታቸው ከነፉ። ተመልሶ ቢመጣ አጣቸው።

PDF Compressor Free Version

፱

ሊቁ ፋሬስ ተዋነይ በጥበቡ ስለ ሰመራት ውኃ ከተናገሩ በኋላ ነበልባል እንዲት ቀን ተኝቶ አላደረም። ሴናማ እንቅልፍ ሰመተኛት ትኑን መራት ሲያስነካ በአእምሮው ቅዠት ለቀቀበት። "የኔታዬ! ወደ ትውልድ ሀገሬ መመለስ እፈልጋለሁ። ከታቦር ውኃ መጽውተው ይሸኙኝ። የመባዛት የርስዎን ቅኔ ፈልጌ አይደልም። በቅኔው እንደሆነ እኔም አንድ ጊዜ ነበልባል ተብያለሁ። ማዕበል መባል ደግሞ አልፈልግም። ነበልባል ይበቃኛል።" እያለ ይለፈልፍ ጀመር።

ነበልባል በቀለም በኩል ነጁ-አሳት ነው። እንደ ስሙ ነበልባል ነው። ስሙንም ነበልባል ብለው በሊቅ ስም የጠሩት ራሳቸው ሊቁ ፋሬስ ድንቁ ናቸው። በመጣ ሰሞን ቅኔዉን ሲያንበሰብሰው ተመልክተው ነበልባል የሚል ስም አወጡለት።

ኃላም ስለ ታቦር ሲቆሻሸ ሲሰሙ፣ ቅዠቱ ለእብደት ሊዳርገው ጥቂ እንደ ደረሰ ሲመለከቱ በነበልባል ሊጫኩት አልፈለጉም-ሊቁ። በታቦር ምክንያት አብዶ ጨርቁን ከሚጥል ሊተባበሩት ፈለጉ። እናም ከዚያ ሁሉ ወፈ-ሰማያት ተማሪ ለይተው አቀረቡት። ከቤታቸው እንዲወጣ እንዲገባ ፈቀዱለት። የምሥጢራቸው ተሣታፊ የቅኔ ዘራፊ አደረጉት። እሱም እግራቸውንና ልብሳቸውን እያጠበ ለመምህራን በሚገባ ክብር ተንከባከበ አገለገላቸው። ቅኔውና ትሕትናው ከፀቅማቸው በላይ ሲሆን የታቦርን ምሥጢር በአፉል ሊነግሩት ጀመሩ።

"ወደ ፊት ከኔ አትለይ። እግዚአብሔር ከፈቀደ በነንድ ደብረ-ጥበብ ካለችዋ የጥበብ ምንጭ ልትጎነጭ ትችላለህ።" ብለው ስለ ታቦር ፍንጭ

PDF Compressor Free Version

ሰጠቻቸው ይህንን ታሪክ ከሰሙ በኋላ አንዳች ነገር ቀለለው። ማታ ማታ በእንቅልፍ ዓለም ሆኖ ስለ ታብር ያስወሸከተው የነበር የምኞት መንፈስ ጥሎት ጠፋ። ቅዠቱ አቆመ። በደንብ ወደ ጤናው ሲመጣ ወደ ፊት ራሳቸውን እንደሚተካቸው አሰበ።

እናም ከዕለታት ባንድ ቀን ተያይዘው ወደ ታብር መረዱ። ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው ‘ታያርያ’ የተባለውን መጽሐፈ-ጥበብ በተሰመረችው ደሴት ፊት ለፊት ገለጡት። ብርሃኑ የዋሻውን ጨለማ ሲበረግደው ደሴቷ ‘ታያርያ’ የተባለውን መጽሐፍ ቅርፅ ይዛ ብልጭ አለች። ነበልባል የብርሃን ምንጭ የብርሃን ፈለግ በውልቅ ቡልቅ ሰትል ከጠባቧ ደሴት ውስጥ በዐይኑ ተመለከተ።

ከዚያም ሊቁ በአጠገቡ ተናገሩ።

“ሊሊት ሴሊት በሕልምህ እንደ ሰይጣን እየመጣች የምታስፈልፍህ ይች ናት። ታብር ትባላለች። ቀደምት የሃንጅ ሊቃውንት ‘ታብር ከሣቲተ-ምሥጢር’ ሲሉ ያወድሷታል። ሐሸማሉች ደግሞ ‘ታብር መክሥተ-ጥበብ’ ይሏታል። ዐይተዋት ግን አያውቁም። እኛ ባለ ቅኔዎች ግን” አሉ ሊቁ ፋሬስ በአመልካች ጣታቸው ወደ ራሳቸው እያመለከቱ።

“እኛ ባለቅኔዎች ደግሞ ታብር ከሣቴ ቅኔ፣ ታብር የቅኔ ምሥጢር እያልን እናሞካሻታለን።”

ነበልባል ራሱንም ሆነ ሊቁ ፋሬስን ማመን ተሣነው። በሕልሙም ሆነ በእውኑ የተመኛትን ምሥጢራዊት ምንጭ በቀላሉ በማየቱ ውስጡ በፍሥሓ ተዋጠ።

PDF Compressor Free Version

ሊቁ "ቀጠሉ ከጸንዐ ዴዴሃ ይበልዕ ፍሬሃ" ነው:: ከፍሬዋ ለመብላት ከፈለግህ ደጅ ጥና" ካሉ በኋላ እሱን ወደ ቅኔ ቤት እንዲመለስ አዘዙ:: ሊቁ ፋሬስ ደሴቷ በር ላይ ቁመው እንደ ከሠቷት መልሰው ሰወሯት:: ብርሃኑ ወደ ጨለማ ነበልባል ወደ ቅኔ ቤት ተመለሰ::

PDF Compressor Free Version

I

ሊቁ ፋሬስ ተዋነይ በጥበቡ የሰወራትን የጥበብ ደሴት ለነበልባል ከገለጡበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ የሊቁ የጥበብ ጭምጭምታ የቅኔ ቤት ሹክሹክታ ሆነ። ሊቅነታቸው በየቅኔ ቤቱ ባሉ የቅኔ ተማሪዎች ጆሮ ደረሰ። ደሴቲን ከመግለጥ አልፎ እንደ ተዋነይ መልአከ-ሞትን ገዝተው በሕይወት የሚኖሩበት ምሥጢራዊ ጥበብ እንዳላቸው በየቅኔ ቤቱ በፀሐይ በጉባይ ተወራ። ይህንን የሰሙ በዐራቱ ማእዘን ያሉ የቅኔ ተማሪዎች ወደ ተዋነይ ሀገር ተመመ። በቅርብ ርቀት የሚገኙት የዋሸራ ማርያም የቅኔ ዘራፊዎች ቁልቁል ወደ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ተንከባለሉ። ሌሎቹም ቀስ በቀስ የቀደመ ቅኔ ቤታቸውን እየፈቱ ጥበብ ለመቃመስ ወደ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ዘመቱ። ከጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቅኔ ቤት ታሪኩ የተባለውን የቅኔ ዘራፊ የቀደመው አልነበረም። አዲማ ጊዮርጊስ ደግሞ ገሞራው ተስተለ። ገሞራው በዲማ ጊዮርጊስ ቆይታው ቅኔና መጽሐፍ ጨርሶ ወደጎንጅ ደብረ-ጥበብ ለመሄድ ከዲማ ጊዮርጊስ ገዳም መምህር ጋር በእንባ ተሰናበቱ። ጉዞው ወደ ጥበብ ሀገር ወደ ጎንጅ ባይሆን ኑሮ፣ ከዲማ ጊዮርጊስ ርቆ መኖር አይፈልግም ነበር። ይልቁንም ከዲማው መምህር ጋር እንዲህ በቀላሉ መራቅ አይታሰብም። ዲማ ጊዮርጊስ በነበረበት ወቅት የዲማው መምህር 'የኔ ይቅርብኝ የኔን ፈንታ አንተ እየበላህ ተማር' ብሰው ከገዳሙ የሚሰጣቸውን የዕለት እራት ለገሞራው እየሰጡ መምህሩ ጦም እያደሩ አስተምረውታል። በዲማ ውስጥ እድሜ ጠገብ የሆኑ መጻሕፍትን እንዳሻው ያለከልካይ እንዲመረምር ፈቅደውለታል። በትርፍ ጊዜ ደግሞ መጽሐፈ-አዳርን

PDF Compressor Free Version

የመሳሰሉ መጻሕፍትን ከራታቸው ቁጭ ብሎ እንዲያነብ ገጸ ሰጥተውታል። እንዳንድ ውድ ውድ ምሥጢራትንም መምህሩ አስተጽሰውታል። እኒህን ሊቅ በእንባ ጠብታ ተሰናብቶ ጉዞው ወደጥበብ ሀገር ሆነ። ወደተዋነይ ቅኔ ቤት። ወደ ፋራስ ድንቁ መንደር። ወደታላቁ ምሥጢር። የጥበብ ሀገሯ መዓት ነው? እያለ ወደ ጎንጅ ደብረጥበብ ገሠገሠ። ጉዞው ከምሥራቅ ጎጃም ወደምዕራብ ጎጃም ወደ ባሕርዳር አቅጣጫ ሆነ። ከዲማ ጊዮርጊስ ተነሥቶ ክራ አቦ ሲደርስ ምድር መሸ። ፀሐይ ወደ አድማስ ተቃረበች። ከክራ አቦ በኋላ ቀጥታ ወደ ፊት ቢገሰግስ ኑር ጉዞው ወደ ባሕር ዳር ሊሆን ነበር። ክራ አቦ ደርሶ ወደ ቀኝ ወደጎንጅ ደብረጥበብ መታጠፍ ነበረበት። እናም የጥበብ ሀገሯ ጎንጅ ነውና ክራ-አቦ ሲደርስ እንደ ያዕቆብ ምድር መሸበት። ገዘ አለረበት።

ክራ አቦ ከኮረብታው ላይ ፊጥ ብላ ያለች አፈ-ቆላ ቢሆኑ የገጠር ከተማ ናት። ከባሕር ዳር ወደ ሞጣ ሊመጡ በግምት ሥልሳ ኪሎ ሜትር አካባቢ ርቃ ትገኛለች። ወደ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ቅኔ ለመማር የሚገሰግሱ የቅኔ ተማሪዎች የጉዝ ማሳረፊያ ደረቅ ወደብ ናት-ክራ አቦ። በእርግጥ የጉዝ ማሳረፊያ ደረቅ ወደብ ብቻ አይደለችም። የቅኔ መዘራረፊያ መካነ-ጥበብ ጭምር እንጂ። የቅኔ ተማሪዎች ከግሪካዊቷ ምኵራብ ጋር አንጻጽረው ኢትዮጵያዊቷ አርዮስፋጎስ ይሏታል። ፈለገ-ጠቢባን ማለት ነው። የጠቢባኑ የንተዋነይ የእውቀት ፈለግ ማለታቸው ነው።

PDF Compressor Free Version

ኮሬ አቦን ከዋሽራ ማርያም አፋፍ የሚወነጨፈው የቅኔ ነፋስ ያናውጻታል። ቅጠሎቿ በቅኔው ወላፈን ተኮማትረዋል። ከቅኔ ሊታውንት አልፎ ተርፎ የኮሬ አቦ ባላገሮች በቅኔ በኩል አይታሙም። የግእዙን ቋንቋ እንደአማርኛ ቋንቋ አቀላጥፈው ይናገራሉ። ውሽክሽክ ቂስ የግእዝ ንባብ ሲያበላሽ ይጠቃቀሱበታል። አንደበቱ ሲወላከፍ በጭብጨባ ዝም አሰኝተው ይመልሱታል-ባላገሮች። ቅኔ-ማኅሌት ቱመው እያስቀደሱ ቤተ-መቅደስ ያለውን ውሽክሽክ ቂስ ክቀሰም ሲናጠብ ማረም የሰንበት ቀን የዕረፍት ሥራቸው ነው።

የኮሬ አቦ ባላገሮች ክሰኞ እስክ ዐርብ ሠርተው፣ቅዳሜ ነግደው አትርፈው፣ በሰንበት ትላላቅ የአቦጀዴ ቅዳጅ ደግልለው፣ ቆሮ ቂስ መስለው ለቅዳሴ ብቅ ሲሉ ውሽክሽክ ቂስ እንደጦር ይፈራቸዋል። ራስ በራሳቸው እንደቄሶች "ርእሰ-ደብር፣ ቂሱ-ገበዝ" እየተባባሉ ሲቀላለዱ ቀልብ ይሰባሉ ባላገሮች። በቅዳሴ ጊዜ በግእዝ ተሰጥዎ ይቀበላሉ። በሽንብራው ማሳ፣ በጤፉ ቃርማያ፣በጤፉ አውድማ፣ የአማርኛ መወድስ ከአፋቸው የማይለያቸው ባላገሮች፣ ከገጠር ቂስ የበለጠ የቅኔ ጠበብት ናቸው። ከባህላዊ ዘፈናቸው ከሚስረቀረቀው ፉጨታቸው፣ ከሚያስፈራራው ፉከራቸው፣ እንደወባ ከሚያንዘፈዝው ሽለላቸው ይልቅ የቅኔ ሽለላ ይቀናቸዋል።

ደናግል ሴቶች ልጆቻቸውስ ቢሆኑ? በቅኔ በኩል ማን እንደነሱ!። በመጣሬያ ደብተራቸው ዳርና ዳር የአማርኛ ቅኔ ጽፈው ይሸመድዳሉ። ከዘመናዊ ትምህርት ጎን ለጎን ግእዝ እያጠኑ ለዐቅመ-ሔዋን ይደርሳሉ።

PDF Compressor Free Version

ሴቶች ለዐቅመ-ሔዋን ወንዶች ለዐቅመ-አዳም ሲደርሱ ቅኒያቸው ለዐቅመ-መወድስ ይደርሳል። በቅኔ በከል ክልስ እመይቱ ገላነሽ ናቸው። ከሀብታም ምጣድ የማትሰፋው ኮሬ አበ ሁለት ተመጋገቢ ነገሮችን ማግኘት የዘወትር ሥራዋ ነው። በላይ ባፋፉ የዋሸራን ሰምና ወርቅ ቅኔ ነፋስ እየገፋ እየገፋ አምጥቶ ኮሬ ላይ ይዘረግፈዋል። የጎንጂን መወድስ የቆላ ነፋስ እየገፋ አምጥቶ ኮሬ ላይ ሲደርስ ይተፋዋል። የሀብታም ምጣድ የምታክለዋ ኮሬ በዚህ ታድላለች። ከባሕር ዳር ምሥራቃዊ ክፍል ሥልሳ ኪሎ ሜትር ርቃ በቅኔ ራስ ገዝ የምትተዳደረዋ ኮሬ አበ አፋፉ ላይ ጉብ ብላ የቅኔ ጅራፍ ይፈዝዛታል። የቅኔ ነፋስ ይነፍስባታል።

ከምሥራቅ አቅጣጫ የሰሊን አኮፋዳ አዘነጋትሉ፣ በረጅመ ጠምጥሞ አንድ ተማሪ ኮሬ አቦን እየተሸከረ ይጠባል። የኮሬ-አበ መንደሮችን ሲቃኝ ቆይቶ ሲያክመው ከገዘየው መቻል ካለው ነባር ዋርካ ሥር አርፎ እንደበርበሬ በቀሉ ዐይኖቹ የከተማዋን ውበት፣ የሀገሯን ስፋት፣ የባሳንሮቹን ፍጥነት መመልከት ጀመረ።

ጠማሙ ገሞራው የጎፈረ ፀጉሩ ለብዙ ዓመታት የመነነ ባሕታዊ አስመስሎታል።

ከባሕር ዳር ተነሥቶ ወደሞጣ ተሻግሮ ከሚሄድ አውቶቢስ ሆድ አሞልጮ የወረደው ቀይ ደመ ግቡ ተማሪ ደግሞ አውቶቡሱን ሸኝቶ ኮሬ አቦን መስተሩቅር የተቀቡ በሚመስሉ ዐይኖቹ እየቃኘ ወደዋርካው ተጠጋ።

PDF Compressor Free Version

ገሞራውና ታሪኩ ካባሩን የኮሬ አበ ዋርካ ተደግፈው እንደተሰመደው እንደሆኑ ሀዘኔታቸውን ሊገልጹላቸው አሣረጉ። ታሪኩ ከምዕራብ አቅጣጫ ገሞራው ከምሥራቅ አቅጣጫ ተነሥተው ኮሬ-አበ ላይ ለአንዲት ምሥጢር ተገናኙ። ሁለቱም ገበያው መኻል ካለው ዋርካ ሥር እንዳረፉ ዐይን ለዐይን ተጋጠሙ። መወድስ ለመወድስ ተጋጨ።

ገሞራው ክተማዋን በርበሬ የተረፈቱ በሚመስሉ ዐይኖቹ ሲቃኝ ቆይቶ እንደልማዱ ጥቂት ተመስጦ መጣበት። ዐይኖቹን ጨፈነ። ከተመሥጦው ሲነቃ በቀልድ ቢጤ ለኮሬ አበ አንዲት ቅኔ መወርወር ፈለጎ፤

"እመኒ ጸባብ ሀገረ ጥበብ ኮሬ፤
ከርሠ መሬታ ጥበብ ወላዕሌሃ በርበሬ።" አለ በቀልድ መልኩ። የአማርኛ ትርጉሙም፤

"ምንም ጠባብ ብትሆን የቅኔ-አገር ኮሬ፣
ምድሯ ጥበብ ነው አፈሯ በርበሬ።" እንደማለት ነው።

በእርግጥ ገሞራው ይህንን ቅኔ የወረወረው በአንቱ አይደለም። ኮሬ በበርበሬ ተውጣ አይቶ እንጂ። ኮሬ-አበ ውስጧ በተዋነይ ጥበብ መሞላቷን ተመልክቶ እንጂ። ጠባብነቷም ቢሆን ገሞራው እንደገለጣትና። ከሀብታም ምጣድ አትሰፋም።

ታሪኩ ከተቀመጠበት ድንጋይ ላይ ተነሥቶ "ታሪኩ እባላለሁ። እንተዋወቅ?" አለ መስተፋቅር የተቀቡ በሚመስሉ ጥርሶቹ ፈገግ ብሎ።

"ገሞራው እባላለሁ!" አለ ገሞራው የበለዙ ጥርሶቹን ለመደበቅ እየጣረ። በዚህ መልኩ ተዋወቁ።

PDF Compressor Free Version

ገሞራው በአኩፋዳው ከያዘው ሽንብራ ቆሎ አውጥቶ "ስለ ማርያም አለወደ ታሪኩ እጀቹን ዘርግቶ።

"እመቤቱ ትስጥልኝ" አለ ታሪኩ ሽንብራውን ቆሎ እጅ ነሥቶ እየተቀበለ።

እቅጻቸው ሁለቱም ጎንጅ ቅኔ ቤት ገብቶ ማደር ነበር። ታሪኩን መኪና በየመንገዱ እያቆመ ሰዓት እላፊ እምጥቶ ኮራ-አቦ አፋፍ ላይ ተፋው። ገሞራው በእግሩ እያዘገመ መጥቶ ኮራ አቦ ሲደርስ የጥርስ ቁርጥማት ተቀስቅሶ አላመጠው። ጥርስ ቁርጥማቱን ከአናቱ የወረሰው ሲሆን ሲነሣበት ላምንት ያንፏቅቀዋል።

"ዝወዴት መጥተው ነው አያ-ጓዴ?" አለ ገሞራው ታሪኩን ጠልቆ እየተመለከተ።

"ከጎንደር ነው የመጣሁት" አለ ታሪኩ።

"ዜማ ቤት ነው?" አለ ገሞራው።

"አይደለም። ወደዚህ ወደ ቆላው ወደ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ቅኔ ቤት እንዳሰ ሰምቼ ቅኔ ልቀኝል እየሄድሁ ነው።" አለ ታሪኩ።

"እኔም ወደ እሱ ነኝ" አለ ገሞራው።

"ታዲያ ለምን አብረን አንሂድም?" አለ ታሪኩ።

"ደስ ይለኛል።"

ሁለቱም አብሮ ለመሄድ ተስማሙ።

በመሸል "ያቺ የቀለም ቀንድ ጎንደር እንዴት ናት?" አለ ገሞራው።

"ደኅና ናት" ታሪኩ በደፈናው መለሰ።

"ጎንደር እስካሁን ከልቤ ናት" አለ ገሞራው።

"የጎንደር ልጅ ነህ እንዴ?" አለ ታሪኩ ወደ ገሞራው በደንብ እየተመለከተው

PDF Compressor Free Version

"እኔ እንጃ። ልሆንም ላልሆንም እችላለሁ። እናቴና አባቴ ጣና ዳር በደንገል ጎጆ እየኖሩ ሳለ እኔ ተወለድሁ።" አለ ገሞራው።

"ታዲያ ጎንደርን እንዴት አወቅኻት?" አለ ታሪኩ።

"ጎንደር ሀገር ብቻ አይደለችም። ታሪክ ጭምር ናት። ታሪክ ያነበበ ጎንደርን በቀላሉ ያውቃል። ጎንደር የሊቃውንት ሀገር ናት። ከዓመታት በፊት ጎንደር ደብረ-ብርሃን ሥላሴ ቅኔ ለመማር ሄጄ ነበር። ጎንደር በአታ ለማርያምም የታች ቤት አቋቋም የሚባለውን ተምሬባታለሁ። እልፍኝ ጊዮርጊስ ተቀምጬ የሳንኪውን አቋቋም ቀጽየባታለሁ - ጎንደርን።" አለ ገሞራው።

"እኔም ጉብል ሳለሁ ወደ ጎጃም መጥቼ ቅኔና የግእዝ ቋንቋ ተምሬ ነበር።"

"ታዲያ ዛሬ ድጋሜ ለምን መጣህ?" አለ ገሞራው።

"የዛሬ አመጣጤ ከድሮ አመጣጤ የተለየ ነው። የድሮ አመጣጤ ቅኔ ለመማር ነበር። የዛሬ አመጣጤን ግን..." ታሪኩ ሊናገረው የነበረውን ምሥጢር ወደ ውስጡ ዋጠው። ልብ ለልብ ሊገናኙ ጥቂት ሲቀራቸው መልሰው ተራራቁ።

ታሪኩ ራሱ የተጠየቀውን አድበስብሶ አለፈና፡-

"ከቅኔ ሌላስ? ምን ምን ታውቃለህ? ወደ ሌላም ሀገር ሄደህ ተምረኻል?" አለ

"አዎ! ሌላም ሌላም ተምሬአለሁ።" አለ ገሞራው በትሕትና።

PDF Compressor Free Version

"ሁሉንም የኢትዮጵያን ክፍል አድርሻዋለሁ:: ይህ ቀረኝ የምለው ያለ አይመስለኝም:: ከመጀመሪያው ስጀመር ሸዋ አንኮበር ለመማር ሄጀ ነበር:: የአንኮበር ተራሮቹ፣ ሸንተረሮቹ፣ ገመገሙና ኮረብታው ሁሉ ጥበብ እንደሆነ ተረድቻለሁ::" አለ ገሞራው ዐይኖቹን ጨፍኖ::

"አንኮበር መድኃኔ ዓለም ተምረኻል?" አለ ታሪኩ::

"እዎ ተምሬበታለሁ::"

"እንዲያውም ከዲማ ጊዮርጊስ በፊት አንኮበር ነበርሁ:: የአንኮበር ቀደምት ሊቃውንት የተለየ የትርጓሜ ስልት እንዳላቸው ከታሪክ አንብቤ ወደ ጉባኤያቸው አቀናሁ:: ስደርስ ከጠበቅሁት በላይ ቀለም ተረዳሁ:: አንኮበሮች በአያሌው የሊቃውንት ቁንጮዎች ሲሆኑ ቅኔውን ሲያወርዱት፣ መወድሱን እንደእንዝርት ሲያሾሩት፣ አቋቋሙን ሲሰልቁት፣ መረግዱን ሲወያርዱት፣ መልክዑ-መልኩን ሲያጠላልፉት አንዲት ቀለም ጠብ አትላቸውም:: እነሱን ካየሁ ወዲህ እኔም ተማር! ተማር! የሚል የእውቀት መንፈስ አደረብኝ:: በቅኔው ግፋበት! ግፋበት! በመወድሱ ፈንጭበት፣ በአቋቋሙ ተቃጭበት፣ የሚል መንፈስ መጥቶ ወረረኝ:: የተለየ የትርጓሜ ስልታቸውን በሚገባ አጠናሁ...::" የጥንቶቹ የነ ወልደ ያሬድ የሊቅነት መንፈስ ዛሬም ድረስ አለ አንኮበር ላይ::" አለ ገሞራው::

"ወልደ ያሬድ ደግሞ ማናቸው?" አለ ታሪኩ::

"ወልደ ያሬድ በእምዬ ምኒልክ ዘመን የነበሩ ዐይናማ ሊቅ ነበሩ:: ከሊቅነታቸው ጎን ለጎን ደግነትም ነበራቸው:: እንዲያውም ከቅድስና ማዕረግ የደረሱ ሊቅ እንደ ነበሩ ታሪካቸው ይመስክራል:: በቀለም

PDF Compressor Free Version

በኩልም የሊቅ ልጅ ሊቅ! የምሁር ዘር ምሁር! የገማልያል ልጅ ገማልያል! ናቸው፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"እንዴት? እንዴት? ኧ..ረ.. በድንግል ማርያም ትንሽ ከታሪኩ ቀንጭብልኝ?" አለ ታሪኩ

"ከታሪክ እንደ ተረዳሁት የወልደ ያሬድ የቀለም አባት ገብረ ክርስቶስ ይባላሉ፡፡ እሳት የላሱ ሊቅ ነበሩ፡፡ የቅድስት ሥላሴ የመጀመሪያው የደብር አለቃም እሳቸው ነበሩ፡፡ አለቅነቱም የተሰጣቸው በሊቅነታቸው ነው፡፡ አለቃ ገብረ-ክርስቶስ ወልደ ያሬድን በቀለም ወልደው ዐርፈው ቅድስት ሥላሴ ተቀበሩ፡፡ ቅድስት ሥላሴ ውስጥ በአለቅነትም ሆነ በቀብር የሚቀድማቸው የለም ይባላል፡፡" አለ ገሞራው፡፡

ከዚያም ታሪኩ በደንብ እያዳመጠው እንደሆነ ዐይቶ ገሞራው ቀጠለ፡፡

"ወደ ፊት ያሰብኩት ተሳክቶ ወደሸዋ ከተሻገርሁ በአደባባይ መወድስ ከማበረክትላቸው ቀደምት ሊቃውንት መኻል ገብረ ክርስቶስና ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ እንዲሁም ወልደ ያሬድ ናቸው፡፡ ብቻ ፈጣሪዬ ሐሳቤን ቶሎ ይቋጨው እንጂ አዲስ አበባ ስገባ ወደቅደስት ሥላሴ አምርቼ ለሊቁ መወድስ እዘርፋለሁ፡፡ ወደ አቡነ ጴጥሮስ አደባባይ ወርጀ ለሰማዕቱ እቀኛለሁ፡፡ ወደ ወልደያሬድ መካነ-መቃብር አዲስ ዓለም ገዳም ገስግሼ እሠልሰዋለሁ፡፡ የሩቅ ጊዜ እቅዴ እሱ ነው፡፡" አለ ገሞራው፡፡ ፈጣሪ ሐሳብህን ያሳካልህ!፡፡ "ነገር ግን ለዐረፉ ሰዎች ቅኔ መቀኘት ለምን አስፈለገ?" አለ ታሪኩ የገሞራውን ፍልስፍና በቀላል ዘዴ ለመፈተሽ፡፡

"ሽጋ ጥያቄ ነው!" አለ ገሞራው፡፡

PDF Compressor Free Version

"አንዳንድ ቀልማዳ ባለቅኔዎች መወድስ የሚመጣላቸው በሕይወት ላሉ ባለሥልጣናት ብቻ ነው። ባለሥልጣናቱ ፊት ጅራታቸውን እየቆሉ ቅኔ የሚዘርፉ ቀልማዳ ባለቅኔዎችና ከራሳቸው አንቅተው የማይጽፉ ደራሲያን ከመጡ ወዲህ ሽጋ ቅኔና ብስለት ያለው መጽሐፍ ማንበብ አቁመናል። ከሌላ አምጥተው የሚጽፉ ስለበዙ ሁሉም ነገር ሰዳቦ ብቻ ሆኗል።" ገሞራው ቀልማዳ ባለቅኔዎችን አነጣጠረባቸው።

"ተሰስተኻል! ወንድሜ! ቅኔማ መደረግ ያለበት በሕይወት ላሉት ነው። ያለፉትማ አልፈዋል። ነፍስ ይማር እንጂ መወድስ ምናቸው ነው?" አሰ ታሪኩ ውስጡን ነክቶት ብዙ ለማናገር።

"በሕይወት ላሉ ቅኔ አያስፈልግም እያልሁኮ! አይደለም። ክብራቸውን የሚገልጥ ቅኔ ይገባቸዋል። እኔም በግሌ መወድስ እየዘረፍሁ ሳወድሳቸው ኑሬአለሁ። ወደፊት ግን ቅኔዬ ከእኒህ ቀልማዳ ባለቅኔዎች ጋር እንዲመሳሰል አልፈልግም። እሱን ለግልቦች ትቸዋለሁ። ወደፊት ቅኔውንም የምቀኘው ለስሜት ወይም ለውዳሴ ከንቱ አይደለም።" አለ ገሞራው።

"ታዲያ እንዴት ነው?" አለ ታሪኩ በመገረም።

"በሕይወት ላሉ መወድስ ስዘርፍ፡ ጮክሩ ዝክሩ ሞት አትፍሩ መሸም ለመሞት ነው፡ የሚል መንፈስ ያለው ቅኔ እንዲሆን እፈልጋለሁ። ለስቡን ጨጥሮስ ስቀኝ የሰማዕቱን ሀገራዊ ጀግንነትና ሰማዕትነት በአደባባይ ለመመስከር ነው። ለሁለቱ ሊቃውንት ቅኔ ስቀኝ ደግሞ መላ የሀገር በቀል ሊቃውንትን ክብር በግሌ ለማጉላት ነው" እያሉ ሲያዘግሙ ከራሳቸን አልፈው ከተዋነይ የቅኔ ከተማ ደረሱ።

PDF Compressor Free Version

እነሆ ኩተማዋ በትላልቅ ዋርካዎች ታጅባለች። የተዋነይ የምስክር ወረቀቶች እኒህ ነበሩ። ገሞራው በትልቁ ዋርካ ቅጠል ሳይ ከወዲያ ወዲህ ው..ር.. ው..ር..የሚሉ ተሐዋስያንን እየተመለከተ በተመለሙ ዛፎችን መቃኘት ጀመረ። ወዲያው አንድ ታሪክ በአእምሮው ውልብ አለበት።

ድሮ ከእኒህ ዋርካዎች ሥር አልፍ አእላፍ ሊቃውንት ትልቁን ዋርካ ተከልለው የቅኔውን ፍልስፍና በሕግ ሲቀምሩ በሕሊናው መጡበት። ከዚያም እኒህ የዋርካ ቅጠሎች ከዘመናት በፊት የቅኔና የጥበብ ማማዎች እንደ ነበሩ አሰላሰለ። ወዲህም የግልቡ ዘመን ሳይመጣ የእውቀት መለኪያው *የምስክር ወረቀት* ከመሆኑ በፊት ትልቁ ዋርካ እንደምስክር ወረቀት ሆኖ ያገለግል እንደነበር ትዝ አለው። ያም ማለት በድሮ ዘመን ጎንጅ ቅኔ ቤት የተማረ ተማሪ ወደ ሌላ ቦታ ሰሥራ ሲሄድ የምስክር ወረቀት አልነበረውም። ደብረ ጥበብ ለመማሩ ማረጋገጫ የተዋነይ ዋርካ አክናፍ ስንት ነው? ተብሎ ይጠየቃል። ስድስት ብሎ ከመለሰ በትክክል መማሩ ይረጋገጣል። የምስክር ወረቀቱ እኒህ ሲሆኑ የመ.ያው መለኪያ ደግሞ የተዋነይ ቅኔ አጠጣል ነበር። እንደ ዛሬው የምስክር ወረቀት ግን አልነበረም። ኩተማዋ በሊቁ ቅኔ ቤት ተከባለች። ታሪኩና ገሞራው ከቅኔ ቤቱ ፊት ለፊት ለእንግድነት ጠጋ አሉ። ቅኔ ቤቱ በዝምታ ተውጦ ነበር።

PDF Compressor Free Version

፲፩

ብዙነይ የሰወራት ውኃ ነበልባልን በድጋሜ እንቅልፍ ነሣችዉ። ቶሎ ጠጥቶ እንደ ውኃዋ ከዚህ ዓለም መሰወር ፈልጓል። በዚህ በክሡት ዓለም መኖር ሰልችቶታል። ዓለም በክፈል እጅ እጅ ብላዋለች። ሴሲት ሲተኛ ተስፋ ቆርጦ ይተኛል። ችግሩ ግን በነጋዉ ፀሐይ ስትፈነጥቅ ሌላ ዓለም ይዛ የተፈጠረች ትመስለውና ትንሽ ተስፋ ትዘራበታለች። ወደ ግታ ተመልሶ ሲያስበው ግን ያው ይቺው አሮጌ ዓለም ናት። ስለዚህ መሰወር ያምረዋል።

ትንኩሽቱ ነበልባል የሲቋን ቃል መጠበቅ ሲገባው ውኃዋን ጠጥቶ በስዋሬ የመኖር ተምኔት ገፋፍቶት በነጋታው ሌሊት ከሲቁ ተደብቆ መጽሐፉን ሸክፎ ቅምጫናውን በቡትቶው ሸገጦ ወደ ታቡር ወረደ። ድቅድቁ ጨለማ እስከ ምጽአት የሚገረሰስ አይመሰልም። የታላቁ ዋርካ ክብደት እንደ መልአከ-ሞት ጥላ ረዝሟል። የሊቁ ተማሪዎች በእንቅልፍ ሰምጠዋል። ከደም ለክር ማደ ሰማደ ካለው ነጫት ከሚባል የገጠር መንደር አንድ ውሻ ለብቻው ከጅብ ጋር ይፋለማል። ጋራው ቁንጮ ላይ ቦ.ግ. አልም። ቦ.ግ.. አልም፣ ስልም፣ ቁልጭ እያለች የምትጠፋዋ ኩራዝ ትታያለች። ሰባ ዮና ግን ቤተ-መጻሕፍቱ ውስጥ ቁጭ ብለው ጸሎት ላይ ነበሩ። ከንጂቸው ውስጥ መብራት ይበራል። ድምፃቸው በክፈል ይሰማል። ከነጫቱ ውሻ በቀር የጎንጅ ሰዎች በእንቅልፍ ዓለም ሰጥመዋል።

PDF Compressor Free Version

ነጫት ከሰንጋ ይብረጫል ከሚሉት መንደሮች አንዷ ስትሆን የጅብ መናኸሪያ ቢጤ ናት። ባላገሩ እንደሚያወራው ከሆነ ስሟም በክፉ ቀን አንድ ጅብ አንዷን ሴት ይዞ ሲነጫት ያየ ሰው 'ነጫት! ነጫት! እረ ነጫት! ቶሎ ድረሱ እያለ ስለጮኸባት "ነጫት" የሚለውን ስም ወርሳለች" ይላሉ ታሪክ ነጋሪዎች።

በሊቁ ቅኔ ቤት ቀንቀን በቅኔ ዘረፋ ሌሊት ሌሊት ደግሞ ዜማ ልክና ግስ በማጥናት እንደቀትር ንብ እሚናደፋ ተማሪዎች ያለ ወትሯቸው በእንቅልፍ ዓለም ሰጥመዋል። 'በእንተ ማርያም' ብለው ያመጡትን ቁራሽ ቀምሰው ሁሉም በጊዜ ነበር የተኙት። ነበልባል ጭር ሲል ዐይቶ ከቅኔ-ቤቱ ወደ ግራ ታጥፎ ቁልቁል ሲወርድ ማንም የተመለከተው አልነበረም። ፊት ለፊቱ ከሚታየው 'ነጫት' መንደር ያለው አሮጌ ውሻ ብቻ ቁልቁል ወደ ነበልባል አፉን አሸሞጥሙጦ ያላዝናል። አላገሮ አላዝኖ ተግ ይላል። ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ተግ ተግ ብሎ ይጮኻል። ጋራው ላይ ያለችዋ ነጫት መንደር የኩራዝ ወጋገን ለብዙ ጊዜ ትጠፋና ብልጭ ትላለች። እነ ነበልባል ግን ልብ ያላት አይመስልም። ለዘመናት የጓጓላትን ምንጭ ለመጎንጨት ቋምጧዋል። ምንጯን ጠጥቶ ከፍ ሲል መሰወር። ዝቅ ሲል ተዋነይን መሆን። በጣም ዝቅ ካለ ደግሞ ፋራስን መሆን ነበር ተምኔቱ። ታዲያ ምን ይሆናል! ታብርን እንደ ወትሮው ስታበራ አላገኛትም። ሰውራ ጠበቀችው።

ነበልባል ከአፈርሁ አይመልሰኝ ብሎ 'አዋዜ' ከምትባለዋ ተራ ምንጭ አንድ ቅምጫና ቅል ድፍርስ ውኃ ቀድቶ ሰው አየኝ አላየኝ እያለ ወደ ባሕር ዳር ፊቱን አዞረ። ከላይ ነጫት ሰፈር ሆኖ ሲከታተለው የነበር

PDF Compressor Free Version

ባላገር አንዲት ጥይት ሲያስፈሀ የገበዘ-ማርያሙ አገልጋይ አባ ዮና
ትልቁን የደብሩን ደወል ደለቁት። ነበልባል መድረሻ ጠፋው። እንደ
ምንም አመልጣለሁ ሲል በባላገር እጅ ወደቀ። ባላገሮች የፈጥነ
ዐሥረው መረመሩት። ትንፍሽ ሳይል ቀረ። አባ ዮና ድሪቶውን ገልጠው
ሲፈትሹ ለምዘ ከምትባለው ምንጭ የቀዳውን ድፍርስ ውኃ በትልቅ
ቅምጫና ይዞ ተገኘ። አባ ዮና ከታቦር ያመጣው መስሏቸው ተናድደው
ምሥጢር እንዴት እንደወጣ ለማረጋጋጥ ወደ ፋሬስ ሮጡ። ባላገሮች
ታቦት የቀሰጠ መስሏቸው ሁለቱ ሊቃውንት በሌለበት እንደ ደረቀ ቆዳ
ከወንዝ እየዘረዘሩ ቆዳው እስኪላላጥ ገረፉት። ገርፈው ገርፈው
ሲለቃቸው በገለባ ሸፍነው ከዳዋ ውስጥ እንደተገኘች አይጥ በእሳት
ለበለቡት። ስሙን ትንቢት ቀደመው። ነበልባል በነበልባል ተንበለበለ።
ሲቀ ፋሬስ በቀለም ልጃቸው የደረሰውን መከራ መቋቋም አቅታቸው
ለወራት አነቡ። እንደ ዳዊት በእንባ ምንጣፋቸውን አራሱ። እንባቸው
እንደሰን ውኃ ያለማቋረጥ ፈሰሰ። ከታቦር ምንጭ በላይ ተንዠቀዠቀ።
ለመር ያክል ጉባኤ ዘግተው በሰቆቃ ሰነበቱ። ሰቆቃቸውንም 'ሰቆቃው
ፋሬስ' ሲሉ ርእስ ሰጡት። ከሰቆቃቸው ጎን ለጎን ባላገሮችን እንደቆሙ
በእሳት ማቃጠል ፈልገው ነበር። ኋላ ግን ሐሽማላዊነት ተቃወማቸው።
ሐሽማሎች በቀልን በበቀል ደም በደም ማድረቅ ይፀየፋሉ። ፋሬስም
ትርፉ ፀፀት መሆኑን አስበው ተዉት። ቢሆንም ባላገሮችን በቀላሉ
አልለቀቋቸውም። ለፍትሕ አቤት ብለው ቀላል ቅጣት አስጣሉባቸው።
የሆነ ሆነና ነበልባል ደመ ክልብ ሆኖ ቀረ።
"ተማሪ በሞተ በሰባት ዓመቱ፣